# አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3568 | ቅዳሜ ሚያዝያ 3 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# የትንሣኤ በዓልን ስናከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ ይሁን ሲሉ የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

የትንሣኤ በዓልን አስመልክቶ የኃይማኖት አባቶች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል

## የፓርቲዎቹ የምርጫ ቅስቀሳ ሲቃኝ

8





ፎቶ- ከፋይል

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉዓለም ኃ/ማሪያም

## ልጆች፤ ስለ ትንሣኤ በዓል ምን ያህል ታውቃላችሁ?

13




ፎቶ- ከገፀ ድር

የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጽናት ማለፍን ከኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ መማር ይገባል

## ትንሣኤ በትናንት ገጾች

15




ፎቶ- ከገፀ ድር

ቀደምት የህትመት ውጤቶች ስለትንሣኤ በዓል ኃይማኖታዊ ትርጉም እና ማህበራዊ ፋይዳ የሚያስገነዝቡ የይዘት ሥራዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ አድርገዋል።

# ትስስርን ያጠበቁ እጆች

## “በሁሉም በዓላት የምናደርገው የማዕድ ማጋራት ለነዋሪዎቻችን ያለንን ክብር የምንገልፅበት ተግባር ነው”

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

በሳህሉ ብርሃኑ

በዓል ማለት ለራስ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት መቁረስ፣ ለራስ ማብሰል ብቻ ሳይሆን አቅመ ደካሞችን ማሰብ መሆኑን ‘የማዕድ ማጋራት’ ንቅናቄ በተግባር እያሳየን ይገኛል። ከመንግስት ቢሮዎች እስከ የሰፈር ወጣቶች የተዘረጋው ይህ የበጎነት እጅ የአዲስ አበባን ማህበራዊ የትስስር ገመድ በእጅጉ አጥብቆታል።



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የትንሣኤ በዓልን አስመልክቶ ማዕድ አጋርተዋል

በበዓላት ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ የሚታየው የአንድነት ድባብ ከተማዋን ለየት ያለ ገጽታ ያላብሳታል። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “ምክክር ከሕማማም እና ከጨለማ የምንሻገርበት ትንሣኤ ነው”

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)

በመለሰ ተሰጋ

ክረምት የመብረቅና የነጎድጓድ ድምፅ በብዛት የሚሰማበት፤ የባሕርና የወንዞች ሙላት የሚያይልበት፤ ሰማይ ደመናን እንደ ጋቢ ተከናንቦ ፀሐይን የሚጋርድበት ወቅት ነው። ሀገርም አንዳንዴ ዘመኗ እንዳይገለጥ እንደ መብረቅና

ወደ ገጽ 5 ዞሯል








አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የማዕድ ማጋራት ልማዳችንን ይበልጥ እናጎልብተው!

የክርስትና እምነት ተከታዮች የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል በታላቅ ክብርና ደስታ ለማክበር በሚዘጋጁበት በዚህ ወቅት፣ የኢትዮጵያውያን የቆየውና እጅግ ውድ የሆነው የእርስ በርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴታችን በጉልህ የሚታይበት ጊዜ ነው። ክርስትና በመሰረቱ የፍቅር፣ የርህራሄና የመስጠት ኃይማኖት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” እና “የሚሰጥ ከሚቀበል ይልቅ ብፁዕ ነው” በማለት የመረዳዳትን ታላቅነት ያስተምራል። ይህ አስተምህሮ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ዘልቆ በመግባት፣ በደስታም ሆነ በችግር ጊዜ እርስ በርስ የመደጋገፍ ባህል ሆኖ ዘልቋል።

የኢትዮጵያ ታሪክ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ታሪክ ነው። ማኅበረሰባችን በጥንት ጊዜም ቢሆን በድርቅ፣ በጦርነትና በሌሎች አደጋዎች ወቅት እርስ በርስ በመረዳዳት ችግሮችን የመወጣት ልምድ ነበረው። ይህ እሴት በተለይም በበዓላት ወቅት እጅግ ጎልቶ ይታያል። ጎረቤቶች፣ ዘመዶችና ወዳጆች አብረው በመሰብሰብ፣ በመብላት፣ በመጠጣትና በመደሰት በዓላትን ያከብራሉ። ይህ ባህል የአንድነት፣ የፍቅርና የመረዳዳት ምልክት ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ፣ ይህ የመረዳዳት እሴት ይበልጥ ጎልቶ እየታየ ነው። በበዓላት ወቅት አቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችንና የሀገር ባለውለታዎችን ማዕድ የማጋራትና የመርዳት ተግባር እየተስፋፋ መጥቷል። ይህ ተግባር “አለንላችሁ” የሚል ወገን እንዳላቸው እንዲሰማቸው በማድረግ፣ ለብዙዎች ትልቅ ብርሃንና ተስፋ ሆኗል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት እየተከናወነ ያለው አቅመ ደካሞችንና የሀገር ባለውለታዎችን ማዕድ የማጋራት ስራ የሚደነቅ ነው። ይህ ተግባር በበዓላት ወቅት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጊዜያትም እየተከናወነ ይገኛል። ይህም የከተማ አስተዳደሩ ለማኅበረሰቡ ያለውን ተቆርቋሪነትና የመረዳዳት እሴታችንን የማጎልበት ቁርጠኝነት ያሳያል። የማዕድ ማጋራት ፕሮግራሞች አቅመ ደካሞችንና የሀገር ባለውለታዎችን ከመርዳት ባለፈ፣ የማኅበረሰቡን አንድነትና ፍቅር የሚያጠናክሩ ናቸው። በተለይም በመጪው የትንሣኤ በዓል፣ በችግር ውስጥ ያሉ ጎረቤቶችንና ሌሎችንም መደገፍና ደስተኛ ሆነው በዓሉን እንዲያሳልፉ ማድረግ ከከተማ አስተዳደሩ ባለፈ ከእያንዳንዱ ማኅበረሰብ አባል ይጠበቃል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የትንሣኤ በዓልን ምክንያት በማድረግ፤ ለማኅበራዊ ችግር ለተጋለጡ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ጧሪና ደጋፊ ለሌላቸው የሀገር ባለውለታ አረጋውያንና በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች በአጠቃላይ ከ233 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወገኖች ማዕድ ማጋራታቸውም የዚሁ የመረዳዳት ቱባ ባህል አካል ነው፡፡

ማዕድ የማጋራቱ ተግባር በከተማዋ የማዕከል መስሪያ ቤቶች፣ በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ጭምር ተከናውኗል፤ ይህንኑ አስመልክቶ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ “በሁሉም በዓላት የምናደርገው የማዕድ ማጋራት፣ ድጋፍ የሚሹ የከተማችን ነዋሪዎችን ‘ምን ጎደለ?’ ብለን በመመልከትና በመጠየቅ ክፍተታቸውን የምንሞላበት፣ ለነዋሪዎቻችን ያለንን ክብር የገለፅንበት ሰው ተኮር ተግባር ነው” ማለታቸው ይታወሳል፡፡

የኢትዮጵያውያን የእርስ በርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴታችን በትንሣኤ በዓል ወቅት ይበልጥ ጎልቶ መታየት አለበት። በችግር ውስጥ ያሉትን መርዳት፣ ደስታን የጋራ ማድረጊያ መንገድ ነው። በመሆኑም፣ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በመጪው የትንሣኤ በዓል፣ በችግር ውስጥ ያሉትን መርዳትና ደስተኛ ሆነው በዓሉን እንዲያሳልፉ ማድረግ አለበት። ይህ ተግባር የማኅበረሰቡን አንድነትና ፍቅር የሚያጠናክር ከመሆኑ ባለፈ፣ የሀገራችንን ብልጽግናና ሰላም ለማረጋገጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። እርስ በርስ የመረዳዳት እሴታችንን ይበልጥ እናጎልብተው!

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ለመፍትሄው በጋራ እንሰለፍ

**ሰናይ ምግባሩ**

ዓለምን በብርቱ ከፈተኑ ሰሞነኛ ጉዳዮች መካከል ነዳጅ አንዱ ነው። ዳፋው ደግሞ በጦርነት የተሳተፉትን ብቻም ሳይሆን ሌሎችን ሀገራትንም ለዘርፈ ብዙ ችግር እንዲጋለጡ አድርጓል። ሀገራችንም የነዳጅ እጥረቱ ቀጥተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ካሳደሩባት መካከል እንደሆነች መንግስትን ጨምሮ የተለያዩ አካላት ሲናገሩ ተደምጧል። ከዚህ ችግር ለመውጣትም መፍትሔ የሚሆኑ ምክረ ሀሳቦችም ተያይዘው ተነስተዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የከተማዋ ነዋሪ በብዙሃን ትራንስፖርት ይጠቀም የሚል ነው፡፡

የችግሩን መነሻ በውል ከተረዳን፣ መፍትሔ የሆኑ ነገሮች በግልጽ ከተነገሩ እነሱን መፈጸምና ማስፈጸም ደግሞ ከሁሉም አካል የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ይህን እንድል ያደረገኝ በመገናኛ የአውቶቡስ ተርሚናል ያስተዋልኩት ነገር ነው፡፡

በዕለቱ በዚሁ ተርሚናል በርካታ ቁጥር ያለው የትራንስፖርት ተጠቃሚ ሰልፎ ይዞ ትራንስፖርት ይጠባበቃል። ሰልፉ በመታወቂያ የሚገቡ፣ ተቀምጦ እና ቆሞ ለመሄድ በሚል የተከፈለ ነው። ሆኖም በቂ የስምሪት አስተባባሪዎች ባለመኖራቸው ምክንያት አውቶብሶች ሲመጡ ሶስቱ ሰልፎች ወደ አንድ ሰልፍ የተቀየረ እስኪመስል ድረስ ትርምስምስ ይፈጠራል፡፡ ግፊያዎች አሉ፤ በዚህ መሃል የሚወድቅና የሚነሳ አለ፤ ስልኩን ጨምሮ ንብረቱን የሚሰረቅም አይጠፉም፡፡ አልፎ አልፎ ለማስተባበር የሚመጣ ሰው ቢኖርም ሰው ገፍቶት ስለሚገባ ተገቢውን አገልግሎት ማግኘትም ሆነ እንዲሰጥ ማድረግ በእጅጉ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህ መሃል ትላልቅ እናትና አባቶች፣ ህጻናት ልጆች፣ ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኞች በብርቱ ሲፈተኑ መታዘብ ችያለሁ። ይህን አካባቢ ማሳያ አደረግኩ እንጂ በሌሎች አካባቢም መሰል ችግሮች ሊኖር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

ይህ ዓለም አቀፍ ሁነት ምን ያስተምረናል የሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ በእኔ እይታ ልንማር ከሚገባን መካከል ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም፣ አላስፈላጊ ጉዞዎችን ማቆምና የእግር ጉዞን ባህል ማድረግን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የብዙሃን ትራንስፖርት አማራጮችን አሟጥጦ መጠቀምም አስፈላጊ ነው፡፡ ግን ደግሞ ይሄን እንዴት በአግባቡ ማከናወን ይቻላል የሚለው ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ ተገልጋዩ አገልግሎቱን በፍትሐዊነት የማግኘት መብት እንዳለው ሁሉ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዳለበት መዘንጋት የለበትም፡፡ ሲሆን ሲሆን በኢትዮጵያዊ ባህላችን መሰረት አቅመ ደካሞችን፣ ሴቶችን፣ ህጻናትን ማስቀደም፣ መከባበር እና መተጋገዝ ይገባል፡፡ ካልሆነ ሌሎችን እየገፉ የትራንስፖርት አገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር ትክክል አይደለም፡፡

ጉዳዩ የሚመለከታችሁ የመንግስት አካላት ደግሞ ሰው በዚህ መንገድ ቁጥሩ በርከት ብሎ ሲታይ ይህን የሚያስተባብሩ ሰዎችን ቁጥራቸውን ጨምሮም ጭምር በሰልፍና በአግባብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡ ኃላፊነቱን ለሹፌሩና ለትኬት ቆራጭ ብቻ መተው በአገልግሎቱ የሚማረሩ ሰዎችን ቁጥር ከማብዛት የዘለለ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም፡፡ የአውቶቡሶች ምልልስ ላይም ተገቢውን ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተለይ በስራ መውጫ እና መግቢያ ሰዓት በርካታ ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎቱን ይጠቀማሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሰዓት ይህን የሚመጥን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ ላይ በትኩረት ሊሰራ ይገባል እላለሁ፤ እናንተስ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ**

**ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ሄለን ጥላሁን
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የትንሣኤ በዓልን ስናከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ ይሁን ሲሉ የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ

**በጋዜጣው አዘጋጆች**

የትንሣኤ በዓልን ስናከብር ካለን ከፍለን የተራቡትን በማብላት፣ የተጠሙትን በማጠጣትና የታረዙትን በማልበስ የደስታው ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል ሲሉ የኃይማኖት አባቶች መንፈሳዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የዘንድሮውን የትንሣኤ በዓል አስመልክቶ የኃይማኖት አባቶቹ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፣ በዓለ ትንሣኤ የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጫ እና የተስፋችን ማሳያ መሆኑን በመገንዘብ፣ በዓሉን ስናከብር ካለን ከፍለን የተራቡትን በማብላት፣ የተጠሙትን በማጠጣትና የታረዙትን በማልበስ የደስታው ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባልም ብለዋል።



ፎቶ- ከገፀ ድር

የትንሣኤ በዓልን አስመልክቶ የኃይማኖት አባቶች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል

ይህ የተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል እና የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዝዳንት ቄስ ደረጀ ጀንበሩ ለትንሣኤ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን ባስተላለፉበት ወቅት ነው።

በዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የትንሣኤ በዓላችንን ስናከብር ዓለም በከፋቷ ላጨለመባቸው ወገኖች ካለን ከፍለን የተራቡትን በማብላት፣ የተጠሙትን በማጠጣት፣ የታረዙትን በማልበስ የደስታው ተካፋይ እንዲሆኑ በማድረግ ቀኑ ለሁላችንም ፍጹም ብርሃን ሆኖ ይውል ዘንድ ክርስቲያናዊ ግዴታችንን እንድንወጣ ጥሪያችንን በእግዚአብሔር ስም እናስተላልፋለን ብለዋል።

ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በመልዕክታቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱና ከመነሳቱ በፊት ለቅዱሳን ሐዋርያት በተደጋጋሚ አስረድቷቸዋል፤ ስለሆነም ሞትና ትንሣኤው ድንገተኛና የግድ ሳይሆን ታውቆ ያደረገው ውድ እንደሆነ ከዚህ እውነታ እንረዳለን ብለዋል።

የሰውን ምልአተ ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ሰርዞ ሰውን ከሞት ቅጣት ነጻ ለማውጣት ብቃት ያለው ቤዛዊ መስዋዕት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነበረበት፤ ይሁን እንጂ ከዚህ ዓይነት ቤዛዊ መስዋዕት ብቁ የሆነ ከፍጡራን ወገን ስላልተገኘ ራሱ መስዋዕት፣ ራሱ መስዋዕት አቅራቢ ሊቀ ካህናት፣ ራሱ ተቀባይ መስዋዕት አምላክ ሆኖ የቤዛነታችንን መስዋዕት ራሱ በራሱ ለራሱ አቀረበ።

በዚህ ቤዛዊ መስዋዕትነትም እኛን ከሞት ቅጣት ነጻ አደረገን፤ ትንሣኤያችንንም በትንሣኤው አበሰረ፤ በክርስትና ኃይማኖት የሚገኝ ፍጹም ድኅነትና ነጻነት በዚህ ቤዛዊ መስዋዕት ላይ የተመሠረተ ነው። ጌታችን በትንሣኤው ትንሣኤያችንን ሊያበስረን የትንሣኤ ሰዎች ሆነን በመንፈስና በሞራል በማደግ ብርሃናተ ዓለም ልንሆን እንጂ እንደገና የጨለማው ኃይል መሣሪያዎች ልንሆን አይደለም ብለዋል።

ዓለም እንደ አጠቃላይ በጨለማ ተውጣ ስትተረማመስ የሚታየው ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ምርጫዋ ስላደረገች መሆኑን የጠቀሱት ፓትርያርኩ፣ ስለሆነም የእኛ ምርጫ ብርሃን የሆነው እግዚአብሔር እንዲሆን የቤተ ክርስቲያን ዘወትር ጥሪ ነውም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል በበኩላቸው፣ "ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በማስቀደም፣ "በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው እግዚአብሔር ከሁሉ አስቀድሞ የተግባርና የተሞክሮ አምላክ መሆኑን ነው። ይህ ተሞክሮ ደግሞ በልጁ ሥጋ መልበስ ፍጹምነትን አግኝቷል። የክርስቶስ የትንሣኤውም ምስጢር አንድን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የመላውን የሰው ልጅ ሕይወት እንደሚመለከት የምንረዳው በወንጌልና በትንሣኤ የምሥራች ነው" ብለዋል።

በዚህ ቀን ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ኃጢአትና ሞት ድል ተነስተዋል። የመጀመሪያው አሮጌው በኃጢአት የተበከለው ፍጥረት ፍጻሜውን አግኝቶ አዲስ ፍጥረት በክርስቶስ ተጀምሯል። እኛም በዚህ በፋሲካ ቀን አዲሱን የዓለም የመጀመሪያ ቀን እናስታውሳለን። የመጨረሻውንም ቀን በተስፋ እንጠባበቃለን። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር የሚመጣበት ቀን ነው ብለዋል ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል፡፡

> **"ትንሣኤ ጥላቻ በፍቅር፣ መለያየት በአንድነት፣ ሐዘን በደስታ፣ እንዲሁም ሽንፈት በድል የተደመደመበት ስለሆነ፣ በእኛም መካከል ጎልቶ መታየት ያለበት ፍቅር፣ ሰላም እና ይቅር ባይነት ነው።።"**

ትንሣኤን የሚያምኑ ልጆች እንደመሆናችን መጠን ሕይወታችን ደስታንና ተስፋን ያዘለ እንዲሆን ተጠርተናል። በምናደርገው በሕይወታችን ሁሉ የአምላክ ቃል መቃኛችን ሊሆን ይገባል። የአምላክን ቃል የሚቋቋም፣ ቅዱስ መንፈሱን የሚያሳዝን፣ ከክርስትና ሕይወት ያልተስማማ ጥላቻን፣ መለያየትንና መገዳደልን ሁሉ እናስወግድ። በእውነት ፈጣሪያችንንም እንደምንወድ በቃላችንና በሥራችን እናሳይ የሚል ጥሪ አቅርበዋል።

አክለውም፣ በቤታችንም ሆነ በአገራችን የሚገዛን ጌታ አድርገን እንሹመው። ወደ እርሱ በመቅረብ በጽድቅ ሕይወት በመጽናት፣ በሕይወታችን መልካም ምግባርን እናሳይ። ከመላው የአገራችን ሕዝቦች ጋር በመተባበርና በአንድነት እንቁም። በዓሉንም ስናከብር እርስ በርሳችንም ይቅር በመባባል እንደተለመደው ከችግረኞች፣ አስታዋሽ ከሌላቸው፣ በጎዳናና በየመጠለያ ቦታዎች ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በማገዝና በመርዳት መሆን አለበት ሲሉ አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በዓለ ትንሣኤው በአገራችን የተፈጥሮ ጉዳት ላጋጠማቸው መጽናናትን፣ በአገራችንና በመካከለኛው ምስራቅ ባሉት አገሮች የሚካሄዱት ጦርነቶች እንዲቆሙና ሰላም እንዲወርድ፣ ለታመሙት ምሕረትን፣ ላዘኑት መጽናናትን፣ በችግርና በጭንቀት ላይ ላሉ በጌታ መጎብኘትን፣ ለታሰሩት መፈታትን፣ ለተፈናቀሉ ወደ ቀያቸው መመለስን፣ ለተራቡና ለተጠሙ ምግብና ውሃን እንዲሰጥልን፣ የተራራቁትን እንዲያቀራርብልን፣ በአጠቃላይ የትንሣኤው ፍሬ ፍቅርንና ወዳጅነትን፣ ትዕግስትና ትሕትናን የምናሳይበት ያድርግልንም ብለዋል።

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዝዳንት ቄስ ደረጀ ጀንበሩ የትንሣኤውን በዓል አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክታቸው፤ የትንሣኤውን መታሰቢያ በዓል ስናከብር በክርስቶስ ኢየሱስ መከራና ሰቆቃ፣ ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን የዘላለም ሕይወት እንዲሁም እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ በኩል የገለጸውን ወደር የሌለውን ፍቅሩን እያሰብን፣ ዕለቱን እግዚአብሔርን በተሰበረ ልብ በማምለክ እና በማመስገን ማሳለፍ ይኖርብናል ብለዋል።

አክለውም፣ ትንሣኤ ጥላቻ በፍቅር፣ መለያየት በአንድነት፣ ሐዘን በደስታ፣ እንዲሁም ሽንፈት በድል የተደመደመበት ስለሆነ በእኛም መካከል ጎልቶ መታየት ያለበት ፍቅር፣ ሰላም እና ይቅር ባይነት ነው የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

ይህም በፍጹም ቅንነት፣ መከባበርና መደማመጥ እንዲሁም በእርቅ የአገራችንን ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ እና የሕዝባችንን አንድነት በጽኑ አለት ላይ ለማቆም ያስችለናል ያሉት የካውንስሉ ፕሬዝዳንት ቄስ ደረጀ፤ በመካከላችን አሉ የሚባሉ ልዩነቶችን በማስተዋልና በጥበብ ለመፍታት፣ ብሎም የበደልናቸውን ብቻ ሳይሆን የበደሉንንም በይቅርታ ለመቀበልና እውነተኛ ሰላም ለማስፈን ብንሠራ ጥላቻ እየደበዘዘ ፍቅር ግን እየጎለበተ ይሄዳልም ብለዋል።

እግዚአብሔር በቃሉ፣ "'ለድሀ ቸር የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል' ስለሚል የክርስቶስን ትንሣኤ ስናከብር በመካከላችን በልዩ ልዩ ችግሮች ውስጥ ያሉትን ወገኖቻችን በማሰብ፣ እነርሱም ከእኛ ጋር የደስታችን ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ ከፍቅር የመነጨ ልግስና እንድናደርግላቸው ይገባል" ሲሉ አክለዋል።

አያይዘውም፣ በደቡብ ኢትዮጵያ በጋሞ ዞን አንዳንድ ደጋማ ስፍራዎች በተከሰተው ከፍተኛ ዝናብ እንዲሁም የመሬት መንሸራተት 125 ወገኖቻችንን በሞት ያጣን እና በብዙዎችም ላይ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት የደረሰ ሲሆን፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ አሁንም ተፈናቅሎ በመጠለያ ውስጥ ይገኛል። ስለዚህ ሕዝባችን በታላቅ ሐዘን ውስጥ ስለሚገኝ በዚህ ወሳኝ ወቅት ስጦታችንን በተደራጀ ሁኔታ በማሰባሰብ የሐዘናቸው ተካፋይ መሆናችንን በተግባር እንግለጽ የሚል ጥሪ አቅርበዋል።

በተያያዘም የኃይማኖት አባቶች 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፣ ምርጫው የዜግነት መብት መሆኑን ጠቁመው፣ በዚህም በንቃት መሳተፍና ምርጫው በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ እንደሚገባም ተናግረዋል።

# ትስስርን ... ከገጽ 1 የዞረ

በስፋት እየተለመደ የመጣው የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብር፣ የአዲስ አበባን የቆየ የመረዳዳት ባህል ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋገረ ክስተት ሆኗል።

የትንሣኤ በዓልን መነሻ በማድረግ ማንሳት በወደድነው በዚህ ጉዳይ ላይ በበዓል ወቅት አቅመ ደካሞችን ለመርዳት በመንግስትና በግለሰቦች የሚደረገው የማዕድ ማጋራት ሥራ ፋይዳው ምንድን ነው? ማህበራዊ ግንኙነታችን እንዲጠናከር ምን ያህል ያግዛል? የሚሉና መሰል ጉዳዮችን እንዳስሳለን፡፡

በዓልን አስመልክቶ በመንግስት በኩል የሚደረጉ የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብሮች በአቅመ ደካሞች ፊት ላይ ትልቅ ተስፋን ሲያሳድሩ ተመልክተናል። ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጀምሮ እስከ ወረዳ አስተዳደር ድረስ የተዘረጋው ይህ ሰንሰለት፣ በዓሉን ማክበር ለሚቸገሩ ወገኖች ማዕድ ማጋራትን ዋነኛ ተግባሩ አድርጎ ሰንብቷል። የከተማዋ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደሚገልጹትም የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብር ከአንድ ወቅት ድጋፍ በላይ የከተማዋን ማህበራዊ መሰረት የሚያጠናክር ትልቅ የፍቅር መግለጫ ነው።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ "እውነተኛ ብልጽግና የሚለካው በህንፃዎቻችን ቁመት ብቻ ሳይሆን፣ አብሮን ያለውን ደካማ ወገን አንስተን አብረን ለመራመድ ባለን ቁርጠኝነት ነው" በማለት የከተማዋ ነዋሪዎችና ባለሀብቶች ያላቸውን ተካፍሎ የመብላት ባህል ሲያደንቁ ይደመጣሉ።

አክለውም፣ "አዲስ አበባ የሁላችንም ኩራት የምትሆነው ማንም ሳይራብና ሳይጠማ በዓልን በእኩልነት ማክበር ሲችል ነው" የሚለው ጥሪያቸው፣ ዛሬ በየደጃፉ ለሚታየው የሰብአዊነት ንቅናቄ እንደ ትልቅ ስንቅ ሆኗል። ይህ የከንቲባዋ መልዕክት በህዝቡ መካከል ያለውን የአንድነት መንፈስ ከማጠናከሩ ባለፈ፣ አዲስ አበባን የርህራሄና የሰብዓዊነት መዲና ለማድረግ የሚደረገውን ጉዞ የሚያፋጥን የሞራል ጉልበት ሆኖ ቀጥሏል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ የትንሣኤ በዓልን ምክንያት በማድረግ፤ ለማኅበራዊ ችግር ለተጋለጡ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ጧሪና ደጋፊ ለሌላቸው የሀገር ባለውለታ አረጋውያንና በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች በአጠቃላይ ከ233 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወገኖች ማዕድ ማጋራታቸውን አስታውቀዋል።

ይህ ተግባር በከተማችን የማዕከል መስሪያ ቤቶች፣ በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች እየተከናወነ ያለ በጎ ተግባር ነው ያሉት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ "በሁሉም በዓላት የምናደርገው የማዕድ ማጋራት፣ ድጋፍ የሚሹ የከተማችን ነዋሪዎችን 'ምን ጎደለ?' ብለን በመመልከትና በመጠየቅ ክፍተታቸውን የምንሞላበት፣ ለነዋሪዎቻችን ያለንን ክብር የገለጽንበት ሰው ተኮር ተግባር ነው" ሲሉም አክለዋል፤ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት።

ማዕድ ከማጋራት ባለፈ አሁን ላይ በመካከለኛው ምስራቅ ባለው ግጭትና በነዳጅ እጥረት ሳቢያ የሚከሰተውን ጊዜያዊ የኑሮ ጫና ለማቃለልና የገበያ ጉድለትን ለመሙላት፣ ከፍተኛ በጀት መድበን መሰረታዊ ምርቶች በበቂ ሁኔታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ እያደረግን እንገኛለን ብለው፣ በዚህም የምርት እጥረት እንዳያጋጥም በሰራነው ሥራ፣ በከተማችን የተረጋጋ የገበያ ሁኔታ እንዲሰፍን ተደርጓል ብለዋል።

አዲስ አበባ ለሀብታሙም ለድሃውም፣ ለሁሉም እኩል የተመቸች፣ ስራዎቻችንም ማንንም ያልዘነጉ አካታች እንዲሆኑ እየሰራን ሲሆን፣ ከተማዋ እየተቀየረችና እየተለወጠችበት ያለው ልማት በሰው ኑሮና አኗኗር ላይ ለውጥ እያመጣ ያለ ነው። 'መስጠት አያጎድልም' ብለን ባደረግንላቸው ጥሪ መሰረት በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ለሚደረገው ማዕድ ማጋራት ለተባበሩን ልበ ቀና ባለሀብቶች፣ እንዲሁም ድጋፍ ለሚሹ ወገኖቻቸው ሁሌም እየተሽከሙ በጉልበታቸው በበጎ ፈቃደኝነት እያገለገሉ ላሉ ወጣቶቻችን በሙሉ በራሴና በነዋሪዎቻችን ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ ሲሉም አክለዋል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በመልዕክታቸው፣ የትንሣኤ በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ መዳን ፍቅሩን እስከ መስቀል የገለጸበት እና በትንሣኤ የምስራች የተበሰረበት በመሆኑ፣ በዓሉን ስናከብር በታላቅ ፍቅር፣ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖቻችን ያለንን መተሳሰብ በተግባር የምንገልጽበት፣ አንዳችን ለሌላችን የደስታ፣ የሰላም፣ የአብሮነት ምክንያት እንሁን እያልኩ፣ በራሴና በከተማ አስተዳደሩ ስም መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ ብለዋል።

በእርግጥ ይህ የበጎ አድራጎት ስራ በመንግስት መዋቅር ብቻ የተገደበ አይደለም። በጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የየአካባቢው የወጣት ማህበራት፣ ባለሀብቶችና የንግድ ድርጅቶችም የዜግነት ድርሻቸውን በመወጣት ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። "ያለኝን ለወገኔ" በሚል መንፈስ የተከፈቱት ደጃፎችና የተዘረጉ እጆች፣ አዲስ አበባ የሁሉንም ደስታ የምትመኝ ከተማ መሆኗን ማሳያ ናቸው።

ወጣቶች በየመኖሪያ መንደሮቻቸው ተደራጅተው፣ እርስ በእርሳቸው በማዋጣትና ከአካባቢው ነዋሪዎች በማሰባሰብ ለአቅመ ደካሞች በዓልን ማክበሪያ የምግብ ፍጆታ ምርቶችን ያቀርባሉ። ምግብ ከማብሰል ጀምሮ፣ የአረጋውያንን ቤት እስከ ማጽዳትና ማደስ ድረስ የሚዘልቅ ተግባር ያከናውናሉ። ከቁሳዊ ድጋፉ ባለፈ፣ በበዓል ቀን ብቸኝነት እንዳይሰማቸው ከአዛውንቶች ጋር አብሮ በማሳለፍ የሚሰጡት ፍቅር አይተኬ ነው።

ማዕድ ማጋራት ለኢትዮጵያውያን አዲስ ባይሆንም፣ በአዲስ አበባ ደረጃ እንደ ትልቅ ንቅናቄ መወሰዱ ማህበራዊ ትስስሩን እያጠነከረው ይገኛል። ይህም ከተማዋን የኮንክሪት ህንጻዎች ብቻ ሳይሆን፣ የርህራሄና የሰብዓዊነት መዲና ያደርጋታል። በበዓሉ ወቅት የሚታየው ይህ መረዳዳት በዓል ሲያልፍ የሚቆም ሳይሆን፣ በቋሚነት ለሚቸገሩ ወገኖች ደራሽ የምንሆንበት ባህል እንዲዳብር መነሳሳትን ፈጥሯል። ማዕድ ማጋራት ከአንድ ቀን የምግብ ድጋፍ በላይ፣ "እኔ ለአንተ አለሁ" የሚል የፍቅር ቃል ኪዳን መታደሻ ሆኖ ይገኛል።

በየአካባቢው የሚገኙ የወጣት ማህበራት ይህንን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ ተራ ተግባር ሳይሆን እንደ ቅዱስ ተልዕኮ ነው የሚመለከቱት። "በዓል ማለት ለእኛ ለብሶ መውጣት ብቻ ሳይሆን፣ አቅመ ደካማ ጎረቤታችን ስቆ እንዲውል ማድረግ ነው" ይላሉ በየካ ክፍለ ከተማ የሚገኙ በጎ ፈቃደኞች። ወጣት ሄኖክ በዛብህ እንደሚገልፀው በየደጃፉ እያንኳኩ የሚያሰባስቡት እህልና ዘይት ብቻ ሳይሆን፣ ትውልዱን የሚያስተሳስር ትልቅ የሞራል እሴት ነው።

"መጀመሪያ አካባቢ ሰውን ማሳመን ይከብድ ነበር፤ ዛሬ ግን ነዋሪው ራሱ ደጅ ጠንቶ 'ማዕድ አጋሩልኝ' ይለናል" የሚሉት የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወጣት ማህበር አባላት በበኩላቸው፣ ተግባሩ በወጣቱና በነዋሪው መካከል የማይበጠስ የመተማመን ድልድይ እንደፈጠረ በኩራት ይናገራሉ። ወጣት አብዱራህማን ሰይድም፣ "ይህ በየመንደሩ የሚታየው የወጣቶች ተነሳሽነት፣ አዲስ አበባን የርህራሄና የወንድማማችነት ህያው ትምህርት ቤት አድርጓታል" ይላል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ አስራት ንጉሴ ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት በከተማዋ እየታየ ያለው የማዕድ ማጋራት ንቅናቄ የከተማዋን ነዋሪዎች የመረዳዳት አቅም ወደ ተደራጀና ውጤታማ ተግባር የቀየረ ትልቅ ስኬት ነው።

"በጎ ፈቃደኝነት የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ሳይሆን፣ የዜግነት ግዴታና የማንነት መገለጫ እየሆነ መጥቷል" የሚሉት ምክትል ኮሚሽነሯ፣ በተለይም በበዓላት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎችን ከማገዝ ባለፈ፣ በማኅበረሰቡ መካከል ያለውን አንድነትና ወንድማማችነት እንደሚያጸና በአጽንኦት ይናገራሉ።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪው ዶክተር ደረጄ ተሰማም በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ ማህበራዊ ፍትሕን ማረጋገጥ የሚቻለው አንዱ ለሌላው ደራሽ ሲሆን ነው። ባለፉት ዓመታት የታየው የዜጎች ተሳትፎና የመረዳዳት መንፈስ አዲስ ገጽታ እየገነባ ይገኛል። ይህ የአብሮነት ድልድይ ለቀጣዩ ትውልድ ትልቅ ትምህርት የሚሆን የታሪክ አሻራ ስለመሆኑ ያነሳል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለፉት የለውጥ ዓመታት የተመዘገቡት ሰው ተኮር ድሎች፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ከተለመደው የሥነ-ምግባር እሴትነት አውጥተው ወደ ስትራቴጂካዊ የለውጥ መሣሪያነት አሸጋግረውታል።

ከመጋቢት ወር 2010 ዓ.ም ወዲህ የታዩት የለውጥ ፍሬዎች ዋነኛ መገለጫ የሆነው የበጎ አድራጎት ተግባር፣ የማኅበረሰቡን የአብሮነት ስሜት በመቀስቀስ በዜጎች መካከል የነበረውን የኑሮ ደረጃ ልዩነት በሥራና በመተሳሰብ ድልድይነት አጥብቧል። በከተማዋ ባህል እየሆነ የመጣው ማዕድ ማጋራትና የበጎ አድራጎት ተግባር፣ ማህበራዊ ፍትሕ በንግግር ሳይሆን በተግባር እንዲረጋገጥና ዜጎች በከተማቸው ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ጽኑ መሠረት ጥሏል።

በአዲስ አበባ ከተማ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት 13 ቢሊዮን 136 ሚሊዮን 434 ሺህ 921 ብር እና በኅብረተሰብ ተሳትፎ የአካባቢ ልማት ሥራዎች 2 ቢሊዮን 200 ሚሊዮን 466 ሺህ 477 በድምሩ 15 ቢሊዮን 336 ሚሊዮን 901 ሺህ 398 ብር በማሰባሰብ ለህዝብ ጥቅም ማዋል መቻሉን ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለከተማዋ ምክር ቤት ባቀረቡት የ2018 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር አፈፃፀም ሪፖርት አመልክተዋል፡፡

ጉዳዩ ማዕድ ከማጋራት ሻገር ሲልና ከኢኮኖሚ አኳያ ሲታይም፣ ባለፉት የለውጥ ዓመታት የተከናወነው የ45 ሺህ 566 የአቅመ ደካሞችና አረጋውያን ደሳሳ ጎጆዎችን በአዲስ የመተካት ተግባር፣ በመደበኛው የመንግሥት በጀት ሊሸፈን የማይችልን ግዙፍ ወጪ በሕዝባዊ ተሳትፎ የታደገ ታላቅ የሀብት ምንጭ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህ ግዙፍ የቤት ግንባታና እድሳት ሂደት፣ በመደበኛ የኮንስትራክሽን ሥርዓት ሊወጣ ይችል የነበረን በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በማዳን፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያለውን የላቀ የሰው ኃይል ኢንቨስትመንት አቅም በተግባር አሳይቷል።

ማዕድ ማጋራት የአንድ ወቅት ኩነት ወይም የዓመት በዓል ትዕይንት ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም የሚለውም የብዙዎች አስተያየት ነው። ዛሬ በየሰፈሩ የሚታየው የወጣቶች መነሳሳትና የመንግስት ድጋፍ፣ ጠንካራ ማኅበረሰብ ለመገንባት መሰረት ነው። ደስታ የሚረጋገጠው ብቻ በመብላት ሳይሆን አብሮ በመቁረስ በመሆኑ በተግባር የታየው ይህ አጋጣሚ፣ በሌሎች ቀናትም ለጎረቤታችን እንድንደርስ ስንቅ ሊሆነን ይገባል።

አዲስ አበባን የፍቅር ከተማ የሚያደርጋት በህንፃዎቿ መብዛት ሳይሆን፣ በእንዲህ አይነት የማይበጠስ የመረዳዳት ሰንሰለት የታጠረች መሆኗ ነውና ይህ በጎነት ይቀጥል እንላለን።


ፎቶ- ከፋይል
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የትንሣኤ በዓልን አስመልክቶ ማዕድ አጋርተዋል

# “ምክክር ... ከገጽ 1 የዞረ

ነጎድጓድ የሚያስደነግጡ እና የትንሣኤዋ ብርሃን እንዳይታይ በከፍታዎቿ ዙሪያ እንደ ጉምና ጭጋግ ሆነው የሚጋርዱ ብዙ ፈተናዎች አሉባት።

ደራሲ ሊዮ ቶልስቶይ በበርካቶች ዘንድ የሥነ ምግባር ፈላስፋ፣ ማኅበራዊ ሕጸጾችን ተቺ እና የሰው ልጆች የሕሊና ድምፅ በመባል ይታወቃል። የዚህ ሩሲያዊ ደራሲ የመጨረሻ እንደሆነች የሚነገርላት ‘ትንሣኤ’ የተሰኘችው መጽሐፉ እ.ኤ.አ በ1899 ዓ.ም ለሕትመት በቅታለች።

ሊዮ ቶልስቶይ በዚህ መጽሐፉ እንደገለጸው፣ ከኃይማኖቱ አስተምህሮ ባሻገር እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበረሰብ በሙሉ ሞራልና መንፈሳዊ ኃይል ዳግም መወለድ ነው ትንሣኤ። እንደ ክረምት መብረቅና ነጎድጓድ፣ የወንዝ ሙላትና መሻገሪያ ማጣትን የመሳሰሉ ከባባድ ችግሮች ባሉበት ወቅት በልቦናና በሕሊና ትንሣኤ ዳግም መወለድን እና ካሰቡት መድረስን ያህል ምን የሚያስደስት ነገር አለ? ይለናል።

ትንሣኤ መታደስን፣ ፍትሕን እና ተስፋን ያመለክታል። ታዲያ ከትንሣኤ በፊት የሰው ልጅ አሊያም አንድ ሀገር በድህነት፣ በኢፍትሐዊነት ወይም በችግር ብዙ የሕማማት ወቅቶችን ሊያሳልፍ ይችላል።

ወዲህ ደግሞ እርስ በእርስ መደጋገፍ፣ መመካከር እና አንዱ ለአንዱ ከፍታ ከፊት መቆም ከቻለ የሀገር ትንሣኤ ሩቅ አይሆንም። እውነተኛ ብሔራዊ እድገት የሚጀምረው በግለሰብ የሕሊና ትንሣኤ ነውና። የእያንዳንዳችን የሕሊና ትንሣኤ ሲደመር የማኅበረሰብ ትንሣኤ ይሆናል። ተፈጥሮ ከክረምት ወደ ጸደይ እንደምትሸጋገር ሁሉ፣ ማኅበረሰብም ችግርን በምክክር ሲፈታ ሀገራዊ ትንሣኤው እውን እንደሚሆን ሊዮ ቶልስቶይ በልብ ወለድ ድርሰቱ አስታኮ የገሀዱን ዓለም ሀቅ ይነግረናል።

ኢትዮጵያም፣ በሰለጠነ መንገድ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች ጥርስ እያስነከሱ፣ እያመረቀዙ፣ ጦር እያማዘዙ፣ ቂም እያስረገዙ ድንገት እንደ በረዶ በሚወርዱ መከራዎች እየተመታች ቀንና ሌሊቷ ተጨፍኖ ብዙ ክረምቶችን አሳልፋለች።

ረሃብ፣ ጦርነት እና ስንፍናን የመሳሰሉ ክረምቶች በኢትዮጵያ ምድር የትንሣኤዋን ብርሃን ጋርደው ለዘመናት አልፈዋል። እናም ሀገር ትንሣኤ ትሻለች። ፋሲካዋ አሊያም መሸጋገሪያዋ ደግሞ ሁላችንንም ሰቅዘው የያዙ እና ጦር የሚያማዝዙ ችግሮችን በሰለጠነ መንገድ መፍታት የሚያስችለው ሀገራዊ ምክክር ነው።

“ከምንም በላይ ድህነት መራር ነው፤ የኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ድህነትም ይዞት የሚመጣው ዳፋ ብዙ ነው” የሚሉት የሥነ ልቦና ባለሙያውና አማካሪ አቶ ማኀደር ሳልህ፣ በድህነታችን ቀዳዳ ታሪካዊ ጠላቶቻችን እየገቡ እርስ በእርስ አናክሰውናል፣ በስንፍናችን ላይ ሌሎች ሸክሞችንም ጨምረውብናል። ወደ ስልጣኔ ጎዳና እንዳንሻገር እንቅፋት ሆነውብናል። ከዚህ ለመውጣት ደግሞ አለመግባባቶቻችንን በሀገራዊ ምክክር ፈትተን ለሀገር ትንሣኤ በጋራ መቆምና መሥራት አለብን ብለዋል።

ሀገርን ከጥልቅ እንቅልፍ የሚያነቃ ነው



ፎቶ- ከፋይል

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)

የሀገራዊ ምክክር። በመመካከር ችግርን መሻገር፣ የጋራ ከፍታን መጨመር እና ከሥልጣኔ ጋር መወዳጀት ብሎም የሀገርን ትንሣኤ ማብሰር ነው የሀገራዊ ምክክር ዋና ዓላማው።

ታዲያ ትንሣኤ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም የሚሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኃይማኖት መምህሩ መጋቢ ሐዲስ እረጌ አየለ፣ ይልቁንም የክርስቶስ ትንሣኤ ከድል በፊት ያለውን አስቸጋሪ ጉዞን ያመለክታል። ይኸውም ትንሣኤ በመከራ፣ በጽናት እና በመጨረሻም በድል የሚጠናቀቅ ጣፋጭ ገድል ነው። በኃይማኖታዊ አስተምህሮ ትንሣኤ በነጻ የሚሰጥ አይደለም፤ በፈተናዎች የሚገኝ እንጂ። በመሆኑም ኃይማኖታዊው የትንሣኤ አስተምህሮ ለነፍሳችን መታደስና ከፍታ ትልቅ ዋጋ እንዳለው ሁሉ ለሀገራችንም ትንሣኤ ሁላችንም ችግሮቻችንን በምክክር በመፍታት፣ ይቅር በመባባል፣ አንዳችን ለሌላችን መዳን ልንኖር ይገባል ብለዋል።

የሥነ ልቦና ባለሙያና አማካሪ አቶ ማኀደር ሳልህ በበኩላቸው፣ በተመሳሳይ መንገድ ብሔራዊ ምክክር የፖለቲካ ልምምድ ብቻ ሳይሆን፣ መከራን የመጋፈጥ፣ ከእሱ የመማር እና ወደ ዘላቂ መፍትሔዎች የመቀየር የጋራ ሂደት ነው።

በዚህ መነጽር ሲታይ፣ ምክክር የማኅበራዊ ትንሣኤ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ይኸውም ለዘመናት እንቅፋት የሆኑ ችግሮቻችንን የምንቀርፍበት፣ በአዲስ አስተሳሰብና ከፍታ ታላቅነታችንን የምናበስርበት፣ በጋራ ጽናት የሚገኝ እና ዳግም ሀገር የምትወለድበት እንዲሁም በአዲስ አስተሳሰብና ልዕልና የምትነሣበት ትልቅ ዕድል ነው ሀገራዊ ምክክር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መምህር ሰሎሞን ተክሌ እንደሚሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ አስተምህሮ የትንሣኤ ዓይነቶች አምስት ናቸው። እነሱም የክርስቶስ ትንሣኤ፣ ጊዜያዊ ትንሣኤ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ፣ ትንሣኤ ዘልቦና እና ትንሣኤ ዘሕሊና ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ በሕሊና ትንሣኤ የታሰበው በልቦና ትንሣኤ ተግባራዊ ይደረጋል። በሕሊና ትንሣኤ ንስሐ ለመግባት ያሰበ ሰው በልቦና ትንሣኤ ንስሐ ይገባል። በአጠቃላይ መንፈሳውያን መልካምነትን ወደ ተግባር የሚቀይሩበት ሕይወት ነው የሕሊና ትንሣኤ።

ኃይማኖታዊ ትርጓሜው እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዳችን በሕሊናም በልቦናም ልንነሣ ይገባል። ይህ ሲሆን የነፍስ ትንሣኤ ለሥጋም ይተርፋልና የሀገርም ትንሣኤ እውን ይሆን ዘንድ ችግሮቻችንን በይቅርታና በምክክር መፍታት ይኖርብናል ብለዋል።

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉጌታ አስፋው ከግለኝነት ወይም እያንዳንዱ ራሱን፣ ማንነትና ፍላጎቱን ከሚያንጸባርቅበት ወደ ጋራ ማንነት መምጣት የሚቻለው ነገሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ አምጥቶ በመነጋገር ነው። በዚህም የነበሩንን ጠንካራ ጎኖች ወይም አንድነትና ሕብረትን የሚያጸኑ ጉዳዮችን ማጎልበትና ማጠናከር ያስፈልጋል። ሀገራዊ ምክክሩም ይህንን የሚያግዝ ነው ብለዋል።

እንደ ሀገር የነበረን የአንድነት ስሜት እንዲሸረሸር እና ግለኝነት የበላይ እንዲሆን ያደረገው ብዙ ነገር ቢሆንም፣ በተለያዩ ጊዜያት የነበሩና ያሉ የፖለቲካ ልሂቃን የተለያዩ መድረኮችን እና መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም የግል አጀንዳቸውን በማራመድ በመሥራታቸው ጭምር የመጣ ነው። በመሆኑም የጋራ የሆነውን ነገር ማምጣት የምንችለው ክፍተቶቻችን ላይ ሁሉም የሚመለከተው አካል እንዲነጋገርበት ሲደረግ እንደሆነም ተናግረዋል።

ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ ብሔራዊነትን ለመገንባት የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ ነው። ለዚህም እነ ሩዋንዳን የመሳሰሉ የአፍሪካ ሀገራት ተምሳሌቶች ናቸው ብለዋል የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ሙሉጌታ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፣ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ወይም ድል በዋናነት አንዳችን ሌላችንን ስናከብር፣ ስንተዛዘን፣ ስንደማመጥና ስንመካከር የሚመጣ ነው። የነበሩ ቁስሎቻችንን ማከም የምንችለው ካለፈው ትምህርት በመውሰድና ይቅር በመባባል ነው። ሀገራዊ ምክክሩ አንዳችን ሌላ ቦታ ሆነን ችግሩን በመረዳት፣ ቁርሾዎችን ከውስጥ በማውጣት፣ ይቅር በመባባል፣ ዳግም ወደኋላ ላለመመለስ ቃል በመግባት ራሳችንን የምናድስበት ነው።

ታዲያ ድርድርና ሽምግልና የመሳሰሉት የአጭር ጊዜ መፍትሔ ናቸው። ምክክር ግን ረጅም ጊዜ እና በተለይም ለዘመናት የቆዩ ችግሮቻችንን ለመፍታት ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል። በምክክር ብዙ ነገሮች አሉ የሚሉት ኮሚሽነር ዮናስ (ዶ/ር) ለአብነትም ውይይት፣ ምክር እና ጭውውትን መጥቀስ እንችላለን። ውይይት ወደኋላ ተመልሰን ችግሮቻችንን የምናይበት መነጽር ነው። ምክር ደግሞ ካለፈው በመማር ወደፊት እንዴት እናድርግ በማለት ሰዎች ወደፊት የሚያዩበት ነው። ሦስተኛው ደግሞ ሰዎችን እንደ ድልድይ የሚያገናኛቸው ጭውውት ነው። ይህም ሰዎች ልምዳቸውን፣ ተስፋቸውን እና ስጋታቸውን በዝርዝር የሚነጋገሩበት ነው። በመሆኑም እነዚህን ድንቅ ሐሳቦች የያዘው ምክክር ነው።

በመሆኑም ምክክር ነገሮችን ከሥር መሠረቱ በማየት፣ ሰዎች ሌላውን ሐሳብ ሳይቃወሙ እና ሳይንቁ፣ በመተባበርና በመደማመጥ አንዳችን የሌላውን ቁስል ለመፈወስ የምንዘጋጅበት የፈውስ እና የእውነት ፍለጋ ሂደት ነው። ይህም ፈውስ ለሀገር ትንሣኤ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ከዚህ በፊት የነበሩትን ችግሮች በሚገባ በመፈተሽ በጥልቀትና አንዱ ሌላውን አክብሮና ሳይፈራ በሽታውን የሚያወጣበት ሂደት ነው። በመሆኑም ምክክር ለሀገር ፈውስ ነው። ከጨለማ ወደ ብርሃን የሚወስደንም መንገድ ነው ብለዋል።

ትንሣኤ እንደ በዓል የሚከበረው እሑድ ነው። ግን እሑድ ለመድረስ ስቅለት ያስፈልጋል። በመሆኑም መከራው እና ጨለማው አርብና ቅዳሜ ላይ ያለው ነው። ስለዚህም የምክክሩ ትንሣኤ እሑዱ ነው። በመሆኑም የሀገር ትንሣኤ ቀደም ሲል የነበሩትን ለምሳሌ ስቅለቱን፣ መቃብሩን እና ጨለማውን አልፎ የሚመጣ ነው። በመሆኑም “ምክክር ከሕማማት፣ ከቁስለት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የምንሸጋገርበት ትንሣኤ ነው” ይላሉ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)።

ሰሞነ ሕማማትን ስናስብ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ጭንቀቶችን፣ የእርስ በእርስ መገፋፋትን እና መሰል ችግሮቻችንን እንመለከታለን። በመሆኑም የሁላችን ቁስል ማከሚያ መንገዱ ምክክር ነው። ስለዚህ ምክክር የሀገር ትንሣኤ ነው። እንደ ኃይማኖት አስተምህሮ “ክርስቶስ ተነሣ” ብለን መልካም ነገሮቻችንን እንደማናቆም ሁሉ፣ ሕይወት እስካለ ድረስ መከራ ስላለ እንኳን ለወገናችን ቀርቶ ለሚጠሉን ሁሉ ዘወትር ፍቅርን በማሳየት ምክክር ባህላችን ሆኖ መቀጠል አለበትም ብለዋል።

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
Addis Abeba City Administration

# መልካም በዓል



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው በሰላም አደረሳችሁ ይላል።

የሁላችንም ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ፤ የቱሪዝም፣ የንግድ፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የብዝሓነት እና የአንድነት ማዕከል በመሆን የሁለንተናዊ ከፍታ ጉዞዋን በልዕልና እየቀጠለች ትገኛለች።

በሁሉም ዘርፍ ዘላቂና ቀጣይነት ያለዉ ለዉጥ እያስመዘገበች፣ ፕሮጀክት ጀምሮ በጥራት እና በፍጥነት የመጨረስ ተምሳሌት የሆነችውን አዲስ አበባ፣ በተለይም በኮሪደር ልማት፣ በወንዝዳር ልማት እና ለሰው ክብር ቅድሚያ በሚሰጡ ሰው ተኮር ስራዎች ዓለም የሚያስደምም ደማቅ አዲስ ታሪክ በመፃፍ ላይ ትገኛለች።

በፈጣን ለውጥ ውስጥ የምትገኘው መዲናችን፣ የመሶብ አንድ ማዕከልን በማስፋፋት፣ አገልግሎትን በማዘመን የህብረተሰባችን ተጠቃሚነት ለማላቅ ተግተን የምንሰራ፣ እንዲሁም እንደወትሮው አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ውብ፣ ለጎብኝዎቿ ተመራጭ፣ ንፁህና ነፋሻማ፣ ለሁሉም ለመኖር ተስማሚ እንድትሆን በቁርጠኝነት እንደምንሰራ እያረጋገጥን፤ መልካም የፋሲካ በዓል እንዲሆን እንመኛለን።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዓሉ የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት እንዲሆን እየተመኘ፣ አቅም ለሌላቸው ወገኖች ኢትዮጵያዊ የመረዳዳት እና የመተሳሰብ እሴቶቻችን ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪውን ያቀርባል!

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

# እንኳን ለትንሳኤ በዓል አደረሳችሁ

**እያልን በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር እና የጤና እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!**

# ብዙዎች የእናንተን ድጋፍ ይሻሉ!

በዩቱዩብ ቻናል በቀጥታ ስርጭት(LIVE)
የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም



SUBSCRIBE Ethiopian Red Cross

Scan with any bank QR SCANER!
ETHQR
SCAN ME!
Ethiopian Red Cross Society

0997010101
0997060606

Scan to pay

IFRC iraiser
SCAN ME!
Ethiopian Red Cross Society


Siinqee
EMPOWERED. TOGETHER BANK
ሲንቄ ባንክ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች፣
እንኳን ለትንሳዔ በዓል በሠላም አደራሳችሁ እያለ፣
በዓሉ የአንድነት፣ የፍቅር እና የበረከት እንዲሆን ይመኛል።
መልካም የትንሳዔ በዓል!
ሲንቄ ባንክ
በአንድነት ወደ ስኬት!
Siinqee Cards
Siinqee ATM
Siinqee POS
Mobile Banking
Internet Banking
QR-Code
swift code
SINQETAA
Dahabshiil
Ria
WESTERN UNION
EthioDash
www.siinqeebank.com
871


ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የትንሳኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
በአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ህብረተሰቡ ፈጣንና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ በዜጎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሀብትና የጊዜ ብክነት ማስቀረት እንዲሁም ለማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በደንብ መተላለፍ የሚቀርቡላቸውን መዝገቦች በማየት ፈጣንና ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ እንዲሠጡ በማገዝ የአዲስ አበባ የህግ የበላይነትን እና ሰላምና ጸጥታ የተረጋገጠባት ከተማ ማድረግ የተቋሙ ተልዕኮ ነው:: ይህን ተልዕኮውን ለማሳካት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ 121 ወረዳዎች ውስጥ በ112 ወረዳዎች የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ተደራሽ ሆነው ለነዋሪው ፈጣንና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል:: ፍርድ ቤቶቹ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50(5) እና በአዋጅ ቁጥር 31/99 አንቀጽ 5 መሰረት ከብር 5,000 ያልበለጡ ክርክሮችን የመዳኘት የፍትሐ-ብሔር ስልጣን አላቸው:: በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የወጡትን ደንብ ቁጥር 150/2015፣ ደንብ ቁጥር 167/2016 እና በደንብ ቁጥር 180/2017 መሰረት የሚቀርቡላቸውን የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች መርምረው ፍትሐዊ ውሳኔ ይሰጣሉ:: ነገር ግን ፍርድ ቤቶቹ ያላቸው የፍትሐ-ብሔር የዳኝነት ሥልጣን በጣም ውስን መሆኑ አሁን ካለው የተሻለ የዳኝነት አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዳይሰጡ አድርጓቸዋል:: ጉባዔ ጽ/ቤቱ ይህንን ችግር እስከ ወዲያኛው ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ እና አዲስ የአደረጃጀት ጥናት በማገባደድ ወደ ሥራ ለማስገባት አበክሮ እየሠራ ይገኛል:: በዚህ አጋጣሚ ይህ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ባለድርሻ አካላት ህብረተሰቡ በመኖሪያ አካባቢ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብቱ እውን እንዲሆን የበኩላችሁን እንድትወጡ ስንል እንጠይቃለን::
የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆንላቹ ይመኛል::
መልካም የትንሳኤ በዓል!!
በአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ!

# የፓርቲዎቹ የምርጫ ክርክርና ቅስቀሳ ሲቃኙ

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት ኤቢሳ ኪዳኔ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ነዋሪ ነው፡፡ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጸው፣ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ በቀጣይ ‘ለራሴና ለሀገሬ ይጠቅማል’፤ ‘የተሻለ ይሰራልኛል’ የሚለውን የፖለቲካ ፓርቲ ለመምረጥ የምርጫ ካርድ አውጥቷል፡፡ በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ የምርጫ ክርክሮችንም እየተከታተለ ይገኛል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን ፕሮግራምና ፖሊሲ ለህዝብ በግልጽ እያቀረቡና እያስተዋወቁ ነው፡፡ ይህም የትኛው ፓርቲ የህዝብን ህይወት የሚያሻሽል፣ ሀገርን የሚያሻግር ሀሳብ ይዞ እንደመጣ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሞላ ጎደል ስርዓት ባለው መልኩ፣ በመከባበር፣ በመደማመጥ፣ ሀሳብ ላይ ትኩረት በማድረግ በተለያዩ ጉዳዮች ክርክር ሲያደርጉ መታዘቡን የሚናገረው ወጣት ኤቢሳ፣ በምርጫ ቅስቀሳና የምረጡኝ ዘመቻ ወቅትም በዋናነት ሀገርን ከድህነት ለማውጣት ያስችላል የሚሉትን ሀሳብ ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው አንስቷል፡፡

ሌላኛው በአዲስ ከተማ ወረዳ 14 የሚሰሩትና በሸገር ከተማ አስተዳደር ቡራዩ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ጌታሁን ቀንዓ በምርጫ መሳተፍ የዜግነት መብት እንደመሆኑ ‘ለሀገርና ወገን የተሻለ ይሰራል’ ብለው ለሚያስቡት የፖለቲካ ፓርቲ ድምፅ ለመስጠት የምርጫ ካርድ አውጥተዋል፡፡ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሀሳብ እያስተዋወቁና እየተከራከሩ ነው፡፡ ይህም በቀጣይ በተሻለ መልኩ ሀገርን የሚመራ ፓርቲ መምረጥ እንድንችል ይረዳናል። ገዥው ፓርቲ ባለፉት ዓመታት ባከናወናቸው ስራዎች የመጡ ውጤቶችንና በቀጣይ ሊሰራ ያቀዳቸውን ስራዎች፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም የያዙትን ፖሊሲና ፕሮግራም እያቀረቡ ይገኛሉ ሲሉ ምልከታቸውን ተናግረዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች አለን የሚሉትን ፖሊሲና ፕሮግራማቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንድ ተከራካሪዎች ወጣ ያሉና ሌሎችን የሚያስቆጣ ሀሳብ ሲያቀርቡ ክርክሩን ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን እያደረጉ ባሉ የሚዲያ ሰዎች (ጋዜጠኞች) እንዲያስተካክሉና እንዲታረሙ አስተያየት እየተሰጣቸው ክርክሩ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ እንደሚገኝ አቶ ጌታሁን ትዝብታቸውን አጋርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ ለማከናወን የጊዜ ሰሌዳ ይፋ አድርጎ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል። በቅድመ ምርጫው ሂደት የመራጮች ምዝገባ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ፓርቲዎች የምርጫ ማኒፌስቷቸውንና ፕሮግራማቸውን እያስተዋወቁ ይገኛሉ፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ክርክርና የምረጡኝ ቅስቀሳ እያደረጉ ነው፡፡




ፎቶ- ከፋይል

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉዓለም ኃ/ማሪያም

ፎቶ- ከፋይል

ወጣት ኤቢሳ ኪዳኔ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የፖለቲካ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሃን ፕሮግራማቸውንና ፖሊሲዎቻቸውን እንዲያስተዋውቁ፣ የግል ዕጩዎችም አማራጭ ሀሳባቸውን እንዲያጋሩና የምርጫ ቅስቀሳ እንዲያደርጉ፣ ከመራጩ ጋር እንዲተዋወቁ ነጻ የአየር ሰዓት ድልድል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና ጋዜጣ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅስቀሳ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ለመሆኑ የፖርቲዎች የምርጫ ክርክርና ቅስቀሳ ምን ላይ ቢያተኩር ለሀገርና ህዝብ የሚጠቅም ይሆናል? ከዚህ አንጻርስ ምን ዓይነት ጥንካሬና ክፍተቶች እየታዩ ነው? በቀጣይስ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ይጠበቅባቸዋል?

7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ በሁሉም የምርጫው ምዕራፍ የባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በምርጫ ክርክሮችና ቅስቀሳ ወቅትም የፖለቲካ ፓርቲዎች በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 44 ንኡስ አንቀፅ 3 ስለምርጫ ዘመቻ እንደተብራራው፤ አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩነት ተመዝግቦ የመታወቂያ ካርድ ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫው አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደሩም ሆነ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልገው፤ በጽሑፍ በማሳወቅ ብቻ እና ሕጋዊ ግዴታዎቹን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካኝነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥራት ወይም ሰላማዊ ሰልፍ የማደራጀት መብት አለው፡፡ እንዲሁም ለምርጫ ውድድሩ ይጠቅሙኛል ያላቸውን መረጃዎች ከቦርዱ የማግኘት መብት ይኖረዋል። የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ህገ መንግሥቱና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች፣ የመራጮችን መብት፣ የሌሎች እጩዎችን የመወዳደር መብት በማክበር በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና አለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉዓለም ኃ/ማርያም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክርና ስነ ምግባር ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚገልፅ በጋራ የተስማሙበት የስነ ምግባር ደንብ አለ፡፡ ከዚህ አኳያ ደንቡን አክብረው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ክርክርና ቅስቀሳ ሲያደርጉ መከባበርን መሰረት ባደረገ መልኩ መሆን አለበት፡፡ ሀሳብን በሀሳብ መሞገት፣ በተረጋገጠ መረጃ መተቸት፣ ከስም ማጥፋትና ጥላቻ ንግግር መቆጠብ ይገባቸዋል፡፡ ሀሳቡን ትቶ ሰውዬውን ከመሞገት (Againest the person fallacy) መውጣት ያስፈልጋል፡፡ የትኛውም ፓርቲ የሚያቀርበውን ሀሳብ ማጣጣል የሚቻለው በሀሳብ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የግልግል እና እርቅ ባለሙያው ሕዝቅያስ አሰፋ (ፕ/ር) እንደሚሉት፣ የብዙ ፓርቲ ዘመቻዎችና ምርጫዎች የህብረተሰቡን ስሜት በመነካካት ያለፉ ቅሬታዎች፣ አለመጣጣሞች፣ ፍርሃትና ጥርጣሬዎች እንዲያገረሹ እንዳያደርጉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም እንደሚናገሩት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት በፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ችግሮች ተግባራዊ መፍትሔዎች ላይ ያተኮረ ሀሳብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እስከአሁን ባለው ሂደትም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰላማዊ መንገድን መርጠውና ዝግጁ ሆነው በምርጫ ሂዳት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቴሌብዥን መስኮት በመከራከር እያሳዩ ያለው ተሳትፎ፣ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት የሚደገፍና በበጎ ጎን የሚታይ ነው፡፡ በአብዛኛው የፖሊሲ አማራጮችና ዋና ዋና የሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ሀሳባቸውን እያቀረቡ ይገኛሉ። መገናኛ ብዙሃንም ተነሳሽነት ወስደው የምርጫ ክርክሮች መድረክ በማመቻቸት የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰፊው የፖሊሲ አማራጮች እንዲያቀርቡ እየሠሩ በመሆኑ የሚበረታታና በጎ እርምጃ ነው፡፡

በሌላ በኩል “ሁሉም ፓርቲዎች ባይሆኑም አንዳንዶቹ የራሳቸውን ሀሳብ፣ ፖሊሲና ፕሮግራም ማስተዋወቅ ላይ ከማተኮር ይልቅ ግለሰብ ላይ ያነጣጠረ፣ የመወነጃጀልና የመጠቃቃት ዓይነት (against the person fallacy) የሚመስል ነገር ተመልክተናል” የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም፣ ጥልቀት ያለው የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦችን በማቅረብ ረገድም ክፍተት ይታያል፡፡ አንዳንዶች ህዝቡ ሊረዳው በሚችል መልኩ በግልፅ ቋንቋ የተቀመጠ ፖሊሲና ስትራቴጂ አላቸው ብሎ በድፍረት ለመናገር ያስቸግራል። ይዘውት የመጡት ፖሊሲም በትክክል ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ተግባራዊ መፍትሔ ከማቅረብ አኳያም ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ያላቸውን ፖሊሲና ፕሮግራም ግልፅ በሆነ ቋንቋ ለህዝቡ ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳሉ፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም እንደሚናገሩት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ሲያደርጉ ከጥላቻና እርስ በእርስ መጠቃቃት የፀዳ መሆን ይኖርበታል። የምርጫ ቅስቀሳ በፓርቲዎች፣ በተከራካሪዎች መካከል መከባበር፣ የዴሞክራሲ ባህል ለማሳደግ፣ ግልጽ የሆነ የፖሊሲና ስትራቴጂ አማራጭ ለማስቀመጥ ይጠቅማል፡፡ ለመራጩ ህዝቡ ደግሞ ‘ማንን መምረጥ አለብኝ’ የሚለውን ለመወሰን እድል ይፈጥራል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ የዴሞክራሲ ባህል ለማሳደግ፣ ግልጽ የሆነ የፖሊሲና ስትራቴጂ አማራጭ ለማስቀመጥ ይጠቅማል። ለመራጩ ህዝቡ ደግሞ ‘ማንን መምረጥ አለብኝ’ የሚለውን ለመወሰን እድል ይፈጥራል

የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ማንሳት ያለባቸው ሀገራዊ ጉዳዮች በተመለከተ የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም ኃ/ማርያም እንደሚሉት፤ “የሀገሪቱ አንገብጋቢና ትላልቅ የሚባሉ ችግሮች ላይ ትኩረት ማድረግ፣ መውጫ መንገዱን ማንሳትና ማመላከት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የሀገር ሰላምና ደህንነት ቁልፍ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘላቂነት ያለው ሰላምና የተረጋጋ ሀገር ለመፍጠር ምን መስራት ያስፈልጋል? በምን መንገድ ነው የተረጋጋና ጠንካራ ሀገር መፍጠር የሚቻለው ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማለትም የዋጋ ግሽበት፣ የወጣቶችና ሴቶች ስራ አጥነትና መሰል ጉዳዮች ላይ አማራጭ ሀሳቦችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ፍትህና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ የመንግስት አወቃቀርና የፌዴራል ስርዓት አንገብጋቢ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ናቸው” ብለዋል፡፡

በቀጣይ በሚኖረው የምርጫ ቅስቀሳ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ ምግባርን አክብረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው በምርጫው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ህግና ስርዓትን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ምርጫውን የሚያስፈፅመው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና ሌሎች የምርጫ ተቋማት በገለልተኝነት መስራት፣ መገናኛ ብዙሃንም ለምርጫ ቅስቀሳ የሚሰጡት የአየር ሰዓትና አምድም ፍትሀዊነት እንዲሆን ማድረግ ለምርጫው ስኬታማነት ወሳኝ እንደሆነ የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም ያስረዳሉ፡፡

በጥቅሉ የምርጫ ቅስቀሳ ወይም የምረጡኝ ዘመቻዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳባቸውን፣ የፖሊሲና ፕሮግራም አማራጮቻቸውን ለመራጩ ህዝብ ለመሸጥና መራጩም ህዝብ የተወዳዳሪዎችን ማንነት አውቆ መምረጥ እንዲችል ያግዛል፡፡ ከዚህ አኳያ የፖለቲካ ፓርቲዎች መራጩን ለማሳመን በሚያደርጉት ጥረት ከጥላቻ፣ የተፎካካሪን ስብእና ከማቃለልና ማጥላላት፣ ከሀሰተኛ መረጃ መራቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# “በባይተዋርነት ውስጥ የነበረችን ሴት ነገዋን ማሳመርን እንደ ትንሣኤ ነው የምቆጥረው”

## በለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ሰልጥና በስራ ላይ የምትገኝ ወጣት

**በሄለን ጥላሁን**

መራብና መጠማትን ለዓመታት የቅርብ ጓደኛዋ አድርጋዋለች፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ጠግቦ መብላትና የተሻለ ጫማ መጫማት ለእርሷ ቅንጦት ናቸው፡፡ የትምህርቷን ጉዳይ ካነሳች ደግሞ “የምትበላው የላት ትከናነበው አማራት” ይሆንባታል፡፡ ከኢሉባቦር እስከ አዲስ አበባ ድረስ በቤት ሰራተኛነት በተለያዩ ግለሰቦች ቤት ሰርታለች፡፡ “ያሳለፍኩትን ከባድ ጊዜ ተማርኩበት እንጂ ተሰብሬ አልቀረሁበትም” የምትለን ወጣት ቤተልሄም መኮንን (ለዚህ ፅሁፍ ሲባል ስሟ የተቀየረ) በለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ሰልጥናለች፡፡

የእናት፣ የአባት፣ የእህትና የወንድም ጣዕሙን ፈፅሞ አታውቀውም፡፡ ‘ቤተሰቤ’ የምትለው ሰው አልነበራትም። ገና በልጅነት እድሜዋ ክፉና ደጉን ለይታ በማታውቅበት ሁናቴ ወላጆቿን በሞት በማጣቷ ምክንያት በአጎቷ ቤት አድጋለች። “አስተምራታለሁ፤ አሳድጋታለሁ ብሎ ኃላፊነት የወሰደው አጎቴ እድሜዬ ለትምህርት ቢደርስም እንኳን አይደለም ለማስተማር ይቅርና ለማኖር ፍላጎቱ ከእለት ወደ እለት እየተቀዛቀዘ መጣ። ይባስ ብሎ በቤት ውስጥ የስራ ጫና በመፍጠር እንድማረርና እንድጠፋ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል” በማለት ቤተልሄም ተናግራለች፡፡

የእኔ የምትለው የቅርብ ቤተሰብ በዙሪያዋ አለመኖሩን ተከትሎ ከአጎቷ ቤት በመጥፋት ሌላ ሰው ቤት ለመስራት ተገደደች፡፡ ረሃብ፣ እርዛት እና የማይነጉ የሚመስሉ ሌሊቶች በጨለማ ሞገዳቸው ቢያስፈራሯት ችግሩን ለመሸሸጊያነት በጊዜያዊ መፍትሄነት የመረጠችው የሰው ቤትን ነበር፡፡

እንደ ወጣቷ ገለፃ፤ የቤተሰብ ፍቅር ማጣት፤ ጣዕማቸውን ለማወቅ እንኳን እድል አለማግኘቷ በህይወቷ ተስፋ እንድትቆርጥ አድርጎታል፡፡ “የኔ ወላጆች በህይወት ኖረው ቢሆን ኖሮ የአማረ ለብሼ፣ ራቤን አስታግሼ፣ ትምህርቴን ተከታትዬ እንዲሁም የወላጅ ፍቅርን ካለማንም ከልካይ የማገኝበት እድል ይኖር ነበር ብዬ አለቅሳለሁ፡፡ በተለይ በቤተሰብ ልዩ እንክብካቤ እና ፍቅር አግኝተው በሚኖሩ ሰዎች ህይወት እቀናለሁ፡፡ የቱንም ያህል ባለቅስ የቱንም ያህል እራሴን ድባቴ ውስጥ ብከትም ያንን የተመኘሁትን ህይወት ለማግኘት አልቻልኩም፡፡ በትላንትና፤ በይሆን ይሆን በተሟጠጠ ተስፋ ውስጥ መጋለብ ትርፉ መጋጋጥና የቆየ ቁስልን ከመነካካት የተሻለ ትርፍ አልነበረውም” ብላለች፡፡

“በሰው ቤት እያገለገልኩ ትምህርቴን ጎን ለጎን ለመከታተል በማደርገው ጥረት ውስጥ አሰሪዎቼ ፍቃደኛ አልነበሩም። አንዳንዴ ለመማር ከነበረኝ ጉጉት የተነሳ ያሰብኩትን ባለማድረጌ አለቅስ ነበር። እራሴን ለማጥፋትም ከአንድም ሁለት ጊዜ ሙከራ አድርጌያሁ” ስትል ወጣቷ የህይወት ውጣ ውረዱ ምን ያህል ወገብ ያጎብጥ፣ ጉልበት ያርድ እንደነበር ተናግራለች፡፡



ፎቶ- ከፋይል

በለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የሰለጠኑ ሴቶች በአዲስ የሕይወት መስመር ላይ ይገኛሉ

ቤተልሄም በኢሉባቦር በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ ስትሰራ የምትጫማው ጫማ አልነበራትም፡፡ በባዶ እግር እየተጓዘች የጠዋት ብርዱንና የከሰዓት ሃሩሩን ተጋፍጣ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ጥርሷን ነክሳ ተምራለች፡፡ ይሄ ሁሉ ባለበት ለረጅም ሰዓት ቆማ ስለምትሰራ የኩላሊት እንዲሁም የወገም ህመም ገጥሟት እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

ወጣት ቤተልሄም ወደ ማዕከሉ የመጣችበትን አጋጣሚ ስታስረዳ እንደገለጸችው፣ በተለያየ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ስልጠና መዘጋጀቱን መረጃ ሲደርሳት እድሉ እንዲያመልጣት አልፈለገችም። በኤሌትሪክና ቧንቧ ስራ ስልጠና ወስዳለች፡፡ “የወንድ ስራ ነው” በሚል በርካታ ሴቶች ስልጠናውን ለመውሰድ አይደፍሩም፡፡ እሷ ግን ይከብደኛል የምትላቸውን ነገሮች የመጋፈጥ ልምድ አላት፡፡ ለቀጣይ ሕይወቷ የተሻለ እድል ማዕከሉ ይዞ መምጣቱ ብርሃን እንዲፈነጥቅላት አግዟታል፡፡

“በብዙ ውጣ ውረድ እና የህይወትን መራራ ጽዋ ለተጋፈጥን ሴቶች ማዕከሉ ዳግም ተስፋችንን እንድናለመልም አድርጎናል፡፡ በተስፋ መቁረጥና በባይተዋርነት ውስጥ ለነበረች ሴት ተስፋ መስጠት፤ ነገዋን ማሳመር ለእኔ እንደ ትንሳኤ ነው የምቆጥረው፡፡ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከሀጢያት ለማንጻት የፍቅር መስዋዕትነት ከፍሏል፤ የሰው ልጆች መከራም በትንሳኤው ጉልበት ድል ተነስቷል፡፡ ትንሳኤው ከወደቅንበት የተለያየ ችግር መነሳትን ያመላክትልናል። የሰው ልጅ ከወደቀበት ጨለማ ተነስቶ ወደሚደንቅ የብርሃን ጎዳና እንዲጓዝ አምላክ ፈቅዷል፡፡ እኔ የዘንድሮውን የፋሲካ በዓል የማከብረው ከቁዘማዬ በማገገም ነገን በተስፋ የተሞላ ጎዳና እንደሚጠብቀኝ በማሰብ ነው” ብላለች፡፡

እንደ ወጣቷ ገለጻ፣ ማዕከሉ እንደእሷ ላሉት ሴቶች የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂ ነው፡፡ ለስድስት ወር የህይወት እና የስራ ክህሎት እንዲሁም የስነ ልቦና ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከስልጠናው በርካታ ነገር አግኝተናል፡፡ ሴት ልጅ ስልጠናዎችን በበቂ ሁኔታ ካገኘች ከገባችበት ችግር መውጣት፣ በስራዋ ውጤታማ መሆን እና ህይወቷን በተቃናው መስመር ላይ ማስኬድ እንደምትችል ተረድታለች፡፡

“አሁን ላይ በተከራየሁበት ቤት ውስጥ እየኖርኩ እገኛለሁ፡፡ ይህን ለማድረግ የቻልኩበት ደግሞ በማዕከሉ ውስጥ የተሰጠኝን የስራ እድል በመጠቀም ነው፡፡ በለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ የስፖርት አሰልጣኝ በመሆን እንዲሁም የፋይናንስና ግዢ ክፍል ውስጥ በመስራት ላይ እገኛለሁ፡፡ የስፖርት አሰልጣኝነቱን ከማዕከሉ ባሻገር በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ላይም በማስ ስፖርት መርሃ ግብር ላይ ተገኝቼ አሰለጥናለሁ፡፡ ስራዎችን ብዙ ጊዜ በፍላጎትና ደስተኛ ሆኘ እከውናለሁ፡፡ በተለይ ስፖርቱን መስራቴ የወገብ ህመሜ እንዲታገስል አድርጎልኛል፡፡ ከከባድ የስራ ጫና ማረፍ ስለቻልኩኝ ከህመሞቼ እያገገምኩ እገኛለሁ” ብላለች።

ነገን ተስፋ በማድረጓ አዲስ ጎጆ ቀልሳ እየኖረች ትገኛለች፡፡ ከ10ኛ ክፍል ያቋረጠችውን ትምህርት አጠናክራ ቀጥላለች፡፡ አሁን ባለችበት ሁኔታ እጅግ ደስተኛ እና ተስፈኛ ናት፡፡ አብረዋት ከሚሰሩ ሰዎችም ጋር ጥሩ ተግባቦትን በመፍጠር ስራዋን በውጤታማነት እያስቀጠለች ስለመገኘቷ በቅርበት የሚያውቋት ይመሰክሩላታል፡፡

የሺወርቅ ብርሃኑ ትባላለች፡፡ በማዕከሉ ውስጥ ፀሃፊ ስትሆን ከቤተልሄም ጋር በስራ ጉዳይ የሚያገናኟቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ በፍጹም ስነ ምግባርና የስራ ተነሳሽነት ስራዋን የምትወጣ ወጣት ስለመሆኗ፣ “ያላት አቅም ወደ ሌላ የሚጋባ እና በቶሎ የመረዳት አቅሟ ከፍተኛ ነው፡፡ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ስራዋን ከዳር ለማድረስ ትሯሯጣለች፡፡ ያሳለፈችው የህይወት መሰናክል መቼም እንደማያቆማት ይልቁኑም ከእለት ወደ እለት እያጠነከራት መጥቷል” በማለት ምስክርነቷን ገልፃለች፡፡

“በማዕከሉ ውስጥ ሰልጥነው የሚወጡ ሴቶች ያሉባቸውን የቀደመ ችግር አራግፈውና በአዲስ መንፈስ ተነቃቅተው ማየትን የመሰለ ነገር የለም” የምትለው የሺወርቅ እንደ ቤተልሄም ያሉ ሌሎች ሴቶችም በዚህ ልክ ለማደግ ሲጥሩ እንደማየት የሚያስደስት ነገር የለም፡፡ ከዚህ የበለጠ የስራ እድገት እንደምታገኝም ያላትን ተስፋ ገልጻለች፡፡

የለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ዳይሬክተር ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ማዕከሉ በዋናነት ጤናማ፣ ምርታማና የተረጋጋ ከተማን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ሴቷ ትልቁን ድርሻ ትወስዳለች፡፡ ማዕከሉ በተለይም በጎዳና ሕይወት፣ በወሲብ ንግድ እና በሌሎች ማህበራዊ ቀውሶች ውስጥ የነበሩ ሴቶችን መልሶ ለማቋቋም ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ወደ ማዕከሉ የሚገቡ ሰልጣኞች በቅድሚያ የጤና ምርመራ እንዲያከናውኑ የሚደረግ ሲሆን የህይወት ክህሎት፣ የስነ ልቦና እና የሙያ ስልጠናዎችን ያገኛሉ። መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃርም የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመቆያ ክፍሎች፣ የጤና እንክብካቤ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ የሥልጠና ወጪያቸው እንዲሁ ይሸፈንላቸዋል። ስልጠናቸውን ጨርሰው ከማዕከሉ በሚወጡበት ጊዜም ትንሽዬ የማቋቋሚያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ወደ ስራ ከተሰማሩ በኋላ ደግሞ የሙያ እንዲሁም የአስተዳደራዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ዋናው አላማ ሴቷ ከነበሩባት ችግሮች ተላቅቃ በሁለት እግሮቿ እንድትቆም ማስቻል ነው፡፡

እስካሁን በተሰሩ ስራዎች የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ ሂርጳሳ ዶ/ር አስረድተዋል፡፡ በዋናነት በብዙ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ የነበሩ ሴቶች ከኢትዮጵያዊ ስርዓትና እሴት ውጪ ሆነው ይሰሩት ከነበረው ስራ ተላቅቀውና ጤናማ በሆነ ስራ ላይ ተሰማርተው እየሰሩ ይገኛሉ። በላባቸውና በድካማቸው ሰርተው መተዳደር እንደሚችሉ ግንዛቤያቸው አድጓል፡፡ ወንጀልን ከመከላከል አንፃር በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት፣ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን የስርጭት መጠን ለመቀነስ ተችሏል፡፡ በማዕከሉ ጤናማ፣ ምርታማና የተረጋጋ ከተማን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ላይ ትልቅ ተሰፋ ሰጪ ስራዎችን እየከወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባ በኢትዮጵያ ከአዋጅ ቁጥር 1370/2017 አንፃር

ጥበቡ ስማቸው (ዐቃቢ ህግ)

**መግቢያ**

በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ ከውልደት እስከ ሞት ድረስ የሚያልፍባቸው ዋና ዋና የሕይወት ምዕራፎች በሕግ አግባብ ተመዝግበው መያዛቸው ለሀገር ዕድገትና ለግለሰቦች መብት መከበር መሠረት ነው። በኢትዮጵያ የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት የተዘረጋው ለሕጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታቲስቲካዊ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በአግባቡ ለመያዝ ነው። ይህ ሥርዓት እያንዳንዱ ግለሰብ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ሕጋዊ ማንነት የሚያረጋግጥበት ብቻ ሳይሆን፣ መንግሥት ለሕዝቡ የሚያደርጋቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በትክክል ለማቀድ ይረዳል።

## የምዝገባ መሠረታዊ መርሆዎች

ሕጉ እንደሚደነግገው፣ ማንኛውም የሲቪል ምዝገባ ኩነቱ በተከሰተበት ቦታ ወይም በአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ አካባቢ መከናወን ይኖርበታል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ትልቁ ቁም ነገር፣ አንድ የሲቪል ኩነት (ለምሳሌ አንድ ልደት ወይም አንድ ጋብቻ) ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ እንደሌለበት ነው። ምዝገባው የሚከናወነው አስመዝጋቢው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በአካል ቀርቦ መረጃዎችን ሲያረጋግጥ ነው። ሹሙ መረጃውን በቅጹ ላይ ካሰፈረ በኋላ፣ አስመዝጋቢው መረጃው ትክክል መሆኑን በፊርማው፣ ወይም ፊርማ መፈረም የማይችል ከሆነ በጣት አሻራው ማረጋገጥ ይኖርበታል።

## የልደት ምዝገባ

የልደት ምዝገባ የአንድ ሕፃን የዜግነትና የማንነት መታወቂያ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ሕጉ ልደት ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ መመዝገብ እንዳለበት ያዝዛል። በዚህ ምዝገባ ወቅት የሕፃኑ ሙሉ ስም፣ ጾታ፣ የልደት ቀንና ቦታ፣ እንዲሁም የወላጆቹ ዝርዝር መረጃ መመዝገብ አለበት። ወላጆች የልጃቸውን ልደት የማስመዝገብ ቀዳሚ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ ወላጆች በሌሉበት ግን ሞግዚት ወይም አሳዳጊ ይህንን ማድረግ ይችላል።

ልዩ ትኩረት የሚሹት ደግሞ ወላጆቻቸው ያልታወቁ ሕፃናት ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሕፃን ያገኘ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ፖሊስም በበኩሉ በ10 ቀናት ውስጥ ለክብር መዝገብ ሹም በማቅረብ ምዝገባው እንዲከናወን ያደርጋል። በጤና ተቋማት የሚወለዱ ሕፃናትን በተመለከተ፣ ተቋሙ ወዲያውኑ የልደት ማሳወቂያ ቅጽ ለወላጆች የመስጠት ግዴታ ተጥሎበታል።

## የጋብቻና የፍቺ ምዝገባ ሥርዓት

ጋብቻ በየትኛውም ሥርዓት (በኃይማኖት፣ በባህል ወይም በክብር መዝገብ ሹም ፊት) ይፈጸም፣ በሕግ ፊት ዕውቅና እንዲኖረው መመዝገብ ይኖርበታል። በኃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት የተጋቡ ጥንዶች፣ ጋብቻው በተፈጸመ በ30 ቀናት ውስጥ ለክብር መዝገብ ሹም ቀርበው ማስመዝገብ አለባቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ፍቺም በሥልጣን ካለው ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል። ማንኛውም መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም፣ ከፍቺ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም አገልግሎት (ለምሳሌ የንብረት ክፍፍል ወይም የጋብቻ ሁኔታን መቀየር) መስጠት የሚችለው ግለሰቡ ሕጋዊ የፍቺ ምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ብቻ መሆኑን ሕጉ በጥብቅ ያስገነዝባል።

## የሞት ምዝገባና ተያያዥ ኃላፊነቶች

ሞት በተከሰተ በ30 ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት። ሞትን የማስመዝገብ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ከሟች ጋር አብሮ ይኖር በነበረ ሰው ላይ ይወድቃል። ይህ ካልሆነ ግን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፣ ወይም ስለ ሁኔታው የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ሊያስመዘግብ ይችላል።

በአደጋ ምክንያት ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ቢሞቱ፣ አደጋው በደረሰበት አካባቢ የሚገኝ የሲቪል ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ምዝገባውን የማከናወን ኃላፊነት አለበት። ማንነቱ ያልታወቀ አስክሬን ሲገኝ ደግሞ ፖሊስ አስፈላጊውን ምርመራ አድርጎ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ማስመዝገብ ይኖርበታል። የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው የኃይማኖት ተቋማት ወይም ዕድሮችም ለሟች ቤተሰብ የሞት ማሳወቂያ ወረቀት የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

## የመረጃ ጥራትና ክልከላዎች

የሲቪል ምዝገባ ሰነዶች ሕጋዊ ማስረጃዎች በመሆናቸው፣ አያያዛቸው እጅግ ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን አለበት። በምዝገባ ቅጾች ላይ ማንኛውንም ዓይነት ስርዝ፣ ድልዝ ወይም ምህጻረ ቃል መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነው። በስህተት የተበላሸ ቅጽ ካለ "ያልተሠራበት" ተብሎ ተሰርዞ እንዲቀመጥ ይደረጋል እንጂ አይቀደድም።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ሐሰተኛ መረጃ መስጠት፣ እውነተኛ መረጃን መደበቅ፣ ወይም የሌላ ሰውን ማንነት ተጠቅሞ ለመመዝገብ መሞከር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ለውጦ ወይም አስመስሎ መሥራትም እንዲሁ ከባድ ቅጣት ያስከትላል።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ፣ የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት ለአንድ ሀገር ሥልጣኔና ለሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ መሳለጥ የማይተካ ሚና አለው። እያንዳንዱ ዜጋ እነዚህን ኩነቶች በወቅቱና በሕጉ መሠረት በማስመዝገብ የራሱን መብት ከማስከበር ባለፈ ለሀገራዊ የመረጃ ቋት ግንባታ የዜግነት ድርሻውን ሊወጣ ይገባል። መረጃው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዞ መያዙ ደግሞ አገልግሎቱን ይበልጥ ቀልጣፋና አስተማማኝ ያደርገዋል።



የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት ለአንድ ሀገር ሥልጣኔና ለሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ መሳለጥ የማይተካ ሚና አለው። እያንዳንዱ ዜጋ እነዚህን ኩነቶች በወቅቱና በሕጉ መሠረት በማስመዝገብ የራሱን መብት ከማስከበር ባለፈ ለሀገራዊ የመረጃ ቋት ግንባታ የዜግነት ድርሻውን ሊወጣ ይገባል


SIKET BANK
ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች
እንኳን ለብርሀነ ትንሳኤው በሰላም አደረሳችሁ!
በዓሉ የሰላም ፣ የጤና እና የስኬት ይሁንላችሁ!
መልካም በዓል!
ዳምጠው አለማየሁ
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
8342
www.siketbank.com
info@siketbank.com
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!


ሲዳማ ባንክ
Sidama Bank
Together, We Can!
ሲዳማ ባንክ አ.ማ
ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች
እንኳን ለብርሃነ ትንሳዔው
በሰላም አደረሳችሁ ሲል
መልካም ምኞቱን ይገልፃል!!
በዓሉ የጤና፣ የሰላምና የፍቅር
እንዲሆንልዎ ባንካችን ይመኛል፡፡
መልካም ፋሲካ
www.sidamabanksc.com
SDMAETAA
EthioDash
Dahabshiil

## ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የትንሳኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የመሬት ሀብት የከበረና ውስን ሀብት በመሆኑ አጠቃቀሙ በጥንቃቄ ሊመራ ያስፈልጋል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ስለ መሬት ባለቤትነትና ይዞታ ከፖሊሲም በላይ በሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ የሚመራ መሠረታዊ ሀብት ነው። መንግስት ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ ለሕዝብ ጥቅም የሚፈለግ ከሆነ፣ ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ በእጁ ከማስገባቱ በፊት አስቀድሞ ለባለንብረቱ ካሳ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40(8) ስር ተደንግጓል። የመሬት ማስለቀቅን አስመልክቶ ያሉ ዋና ዋና ሕጎች አዋጅ ቁጥር 1161/2011፣ አዋጅ ቁጥር 1336/2016፣ ደንብ ቁጥር 472/2012፣ መመሪያ ቁጥር 79/2014 እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 30/1994 መጥቀስ ይቻላል።

ሁሉም የከተማችን፣ የሀገራችንና የውጪ ሀገራት የዲፕሎማሲ ማህበረሰብ ጭምር እንደሚመሰክሩት ዛሬ ላይ አዲስ አበባ ከተማ እንደገና እንደ አዲስ እየተገነባች ያለች ከተማ መሆኗ እሙን ነው። አሮጌ መንደሮች እየፈረሱ ረጃጅም ሕንፃዎች እየተገነቡ ነው። እነዚህ የሕንፃ ግንባታዎች፣ የልጆች መጫወቻ ቦታዎች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ የሳይክል መንገዶች፣ በአጠቃላይ መዲናዋን ይመጥናሉ የተባሉ ማራኪ ዕይታ ያላቸው ኮሪደሮች እና ሌሎች ሲገነቡ የነዋሪውን ቤትና ንብረት መንካቱ አይቀሬ ነው። በዚሁ ለልማት ሲባል መንግስት የግለሰቦችን ይዞታ ማስለቀቅ ቢችልም ግን ደግሞ ላስለቀቀው ይዞታ ምትክ ቦታ እና ለፈረሰው ንብረት ተገቢውን ካሳ ይሰጣል። ምትክ ቦታ እና ካሳን በተመለከተ የሕብረተሰቡን ቅሬታ ለመቀነስ የጉባኤው ስልጣን ተደራሽነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህ የከተማው ነዋሪዎች የዚህን ጉባዔ ራዕይ ለማሳካት ከተደራሽነቱ አንፃር እንዲሁም ቀልጣፋና ውጤታማ ውሳኔ እንዲሰጥ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ እንድታደርጉ መልዕክቴን ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

መልካም የትንሳኤ በዓል! ስለ ጉባኤው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በWebsite:- www.ulc.gov.et ማግኘት ይቻላል።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ**







MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ

**ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የትንሳኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤ መልካም ምኞቱን ይገልጻል!**

ግሩፑ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በንግድ፣ በሆስፒታሊቲ እንዲሁም በኮንስትራክሽንና ሪል እስቴት ዘርፎች የተደራጁ 45 ኩባንያዎችን ያቀፈና ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የቻለ ነው። ማህበራዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት ከትርፋችን 10 በመቶውን በመመደብ ሀገራዊ ኃላፊነታችንን እየተወጣን እንገኛለን።

በተለያዩ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ መንገድ፣ ንጹህ ውሃ፣ የወንዝ ዳር ልማት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታና ሌሎች ስራዎችን እየሰራን ዜጎችን ተጠቃሚ አድርገናል።
ወደፊትም ለሀገራችን የምናበረክተዉን አስተዋጽኦ አጠናክረን እንቀጥላለን።


# መልካም በዓል

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ- የሀገር ሀብት

# ልጆች፤ ስለ ትንሣኤ በዓል ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በሄለን ጥላሁን**

ልጆች የትንሳኤ በዓል በመላው ዓለም የሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ እና በታላቅ ድምቀት የሚከበር በዓል ነው፡፡ በዓሉ ከመድረሱ በፊት ለሁለት ወራት ያክል በጾምና በጸሎት ይቆያል፡፡ ልጆችዬ እኛም በዛሬው ዝግጅታችን ስለ ትንሳኤ (የፋሲካ) በዓል ምንነት፣ ልጆች በእለት ተዕለት ህይወታቸው ሊተገብሩት ስለሚገባ ጉዳይ የሀይማኖት አባትን ሃሳብ በማካተት እንደሚከተለው አሰናድተንላችኋል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
የሚያጋጥሙ ችግሮችን በፅናት ማለፍን ከእየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ መማር ይገባል

ቄስ መንግስቴ ዋሴ እባላለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማሪያም ገዳም አገልጋይ ነኝ፡፡ በነገው ዕለት የሚከበረው የትንሳኤ በዓል ለህዝበ ክርስቲያኑ ትልቅ ትርጉም አለው። ትንሳኤ ከፈጣሪ ዘንድ ለሰው ልጆች ተስፋ የተቸረበት ነው፡፡

ልጆችዬ፤ ትንሳኤ ማለት፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሃጢያት የከፈለው የመስቀል ላይ ፍቅር ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሃጢያት ሲል ሞተ፡፡ በሦስተኛው ቀን በታላቅ ኃይልና ብርሃን ከመቃብር ተነሳ፡፡ በዓሉ መነሳቱን የምናከብርበት እንዲሁም እኛ የሠው ልጆች ከአባቱ ጋር የታረቅንበት በዓል ነው፡፡

ፋሲካ (ትንሳኤ)፤ ሞት አልፎ ሕይወት መምጣቱን፣ ጨለማው በብርሃን መተካቱን የሚበሰርበት በዓል ነው፡፡ ልጆችዬ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሠው ልጆችን የወደደበት የፍቅር ጥግ የተገለፀበት ነው። በዓሉ የብርሃን ቀንን ያመላክተናል። ይህ ሲባልም ህይወት ከጨለማው ወጥቶ በብርሃን የተሞላበትን የተስፋ ጊዜ ያመላክተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፤ ሞት ተሸንፎ ህይወት የሰለጠነበትን ቀን እንድናስብ ያደርገናል፡፡ የሠው ልጅ ከሃጥያት ነፃ የወጣበትን ቀን የምናስብበት እና የምናከብርበት በዓል ነው፡፡

ልጆች፤ በዓሉ እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች ያደረገውን እርቅ የምናስብበት ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ስርዓቱን በጠበቀ አግባብ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ለእግዚአብሔር የምስጋናና የክብር ውዳሴ ይደረጋል፡፡ ወንጌል ይሰበካል። በመዘምራን አማካኝነት የውዳሴ መዝሙሮች ይቀርባሉ፡፡

ለ55 ቀናትም ስጋ፣ ወተትና እንቁላል ሳይበላ ከተቆየ በኋላ፤ በትንሳኤ ሌሊት ፆም ስለሚፈታ በደስታ እና በፍቅር ቤተሰብ ተሰባስቦ ይመገባል፡፡

በዓሉ የበለጠ ውብና ደማቅ እንዲሆን ሁሉም አቅሙ የፈቀደውን ያደርጋል፡፡ አቅም ያለው ቤተሰብም ለልጆች አዳዲስ ልብሶችን ይገዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በበዓሉ ዕለት ከመብላትና ከመጠጣት ባሻገር የተቸገረውን መርዳት በስፋት የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ለተቸገረ መስጠት እግዚያብሔር የሚወደው ተግባር ነው፡፡

ልጆችዬ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የከፈለውን የፍቅር መስዋዕትነት በመረዳት በዕለት ተዕለት ህይወታችሁም ልትተገብሩት ይገባል፡፡


ልጆች ከዚህ በዓል ልትረዱት አልያም በእለት ተዕለት ህይወታችሁ ልትተገብሩት ስለሚገቡ ተግባራት ጥቂት ልበላችሁ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ፍቅር እና እውነተኛ መስዋዕትነትን ነው፡፡ ይህ ሲባል ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ስለወደደ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቶናል፡፡ ታድያ ከዚህ መማር ያለባችሁ በትምህርት ቤት ውስጥ አልያም በምትኖሩበት አካባቢ ካሉ ወዳጆቻችሁ እንዲሁም ጓደኞቻችሁ ጋር በፍቅር እና በመተሳሰብ መንፈስ ያላችሁን ተካፍላችሁ መኖር ይገባችኋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነስቷል፡፡ ይህም ተስፋንና ዳግም መነሳትን ያየንበት ነው፡፡ እኛ ደግሞ ተስፋ ሳንቆርጥ ነገን ማሰብ ይጠበቅብናል፡፡ በተለይም ልጆች በትምህርታችሁ ተስፋ ሳትቆርጡ በጠንካራ መነሳሳት ጥናታችሁን በአግባቡ በማከናወን ከሁሉም የተሻለ ውጤት የማስመዝገብ አቅም እንዳላችሁ ማሰብ እና ለዚህም በርትታችሁ ማጥናት ይጠበቅባችኋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሯል። ሰላምን የሰጠ አምላክ መሆኑን በማመን ልጆችም ከጓደኞቻችሁ ጋር የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላም መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲባል ቂምንና ጥላቻን በማስወገድ የይቅርታን ልብ በተላበሰ አግባብ ጓደኛነታችሁን ማጠንከር ይገባል እላለሁ፡፡

በበዓሉ ቀን የተቸገሩ ጓደኞቻችሁ ወደ ቤት እንዲመጡ በመጋበዝ አስፈላጊውን ነገር ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡ የደስታችሁ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡ ልጆችዬ ልባችሁን በፍቅርና በይቅርታ የተሞላ በማድረግ ደስተኛ ህይወትን ከመምራት በበለጠ በእግዚያብሔር ዘንድም ተወዳጅ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ራሱ ሳይቀምስ የቆረሰውን ለሌላ ያጎርስ**

**መልስ፡-** ሐ. እጅ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ንፍሮውን ትቼ ገበታውን በላሁት**

ሀ. ጉልባን
ለ. ዱባ
ሐ. ገንፎ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

# የመዲናችን ኪነ ጥበባዊ መረጃዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል መጽሐፍ፣ ፊልም፣ የሥነ ጥበብ አውደ ርዕይ እና ሙዚቃ ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

በወንድሙ ካባው የተዘጋጀው “የጀርባ ገጾች” የተሰኘው አዲስ መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ ደራሲው ለመጽሐፉ “የጀርባ ገጾች” የሚል ርዕስ የሰጠው፣ በውስጡ የሰፈሩት ጉዳዮች በሙሉ ማኅበረሰቡ ወደ ኋላ የተዋቸውና ያሳለፋቸው ትዝታዎች መሆናቸውን መግለጹን የሁነት አዲስ መረጃ ያሳያል፡፡ ይህ አዲስ መጽሐፍ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በተለይም የቤተሰብ መስተጋብሮችን፣ የፍቅር ግንኙነቶችን እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚታዩ የተማሪና መምህር ግንኙነቶችን የሚዳስስ ነው። ታሪኩ ከቤተሰብ አውድ ተነሥቶ በዩኒቨርሲቲ ምርቃት የሚጠናቀቅ ሲሆን፣ በዋግ ሕዝብ ዘንድ የሚታወቁ ለየት ያሉ የግጥም ባህሎችን በመጽሐፉ ውስጥ ማካተቱ ታውቋል። መጽሐፉ የደራሲው የመጀመሪያ የሕትመት ሥራ ሲሆን፣ በቀጣይም ሌላ መጽሐፍ ለንባብ ለማብቃት እየሠራ መሆኑን አስታውቋል።

በተጨማሪም የታዋቂዋ ደራሲ የዝና ወርቁ “እውቀት በጨዋታ” የተሰኘ የልጆች መጽሐፍ በቅርቡ ለንባብ ይበቃል፡፡ መጽሐፉ የቅደመ ህትመት ሽያጭ ላይ ይገኛል፡፡ ደራሲዋ “ልጆች እንዲያነብቡ እንመክራለን፤ በተለይም ከ12 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ለሚገኙ ልጆች የሚሆኑ መጻሕፍት የሉም ሊባል በሚችልበት ደረጃ ላይ ናቸው። በ2004 ዓ.ም ‘መፍቻው እና ሌሎች…’ የሚለውን መጽሐፌን ያሳተምኩት ይኼው ችግር አነሳስቶኝ ነበር። ምክንያቱ ጥናት ባይደረግበትም ችግሩ አሁንም እንዳለ ነው” ስትል መጽሐፉን ለማዘጋጀት የተነሳችበትን ሃሳብ ገልጻለች። በመሆኑም የመፍትሔ አካል ለመሆን በመወሰን 150 (አንድ መቶ ሃምሳ) ገጽ መጽሐፍ ማዘጋጀቷልን ገልጻለች፡፡

## ፊልም

“ዳሎቪያ” ፊልም ለእይታ ሊቀርብ ነው። ተዋናይ ግሩም ኤርሚያስ በዋና ገጸ-ባህሪነት የሚተውንበት ይህ ፊልም በነገው ዕለት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም አዳራሽ እንደሚመረቅ ተገልጿል። ከመጪው ሚያዝያ 09 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ሲኒማ ቤቶች ለዕይታ የሚበቃው ይህን ፊልም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ለአንድ ዓመት ከስድስት ወራት ያህል ከፍተኛ ዝግጅት መደረጉ ተነግሯል፡፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምንና የፊልም ኢንዱስትሪውን ዕድገት ታሳቢ ያደረገው ይህ ሥራ፣ አብዛኛው ቀረጻው የተከናወነው በሻኪሶና አካባቢው እንደሆነ ታውቋል።

## የሥነ- ጥበብ አውደ ርዕይ

የእዮብ ኪታባ የስዕል አውደ ርዕይ ለእይታ በቃ፡፡ “ከጣራ በታች” የተሰኘው ይህ የስዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ የሚገኘው በገብረክርስቶስ ደስታ ሞደርን አርት ሙዚየም ውስጥ ሲሆን፤ እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በእይታ ላይ ይቆያል፡፡

በሌላ መረጃ “በሰማይ እና በምድር መካከል” የተሰኘ የስዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ የሰዓሊ መላኩ አየለ ስራዎች የቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይም እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በእይታ ላይ ይቆያል፡፡ አውደ ርዕዩ የሚታየው ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን መግቢያው በእስጢፋኖስ ቤተክርስትያን በኩል ነው፡፡

እንዲሁም የሰዓሊና ቀራጺ ታምራት ገዛኸኝ ሥራዎች የቀረቡበት “ኩይሳ” የቅርጻ ቅርጽ አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ነው፡፡ ይህ አውደ ርዕይ ከተለያዩ የወዳደቁ ቁሳቁሶች የተሰሩ ልዩ የጥበብ ውጤቶች ለተመልካች የቀረቡበት ሲሆን፤ ለቀጣይ ሁለት ሳምንታት በእይታ ላይ እንደሚቆይ ተገልጿል፡፡ ይህ የቅርጻ ቅርጽ አውደ ርዕይ የሚታየው ብስራተ ገብርኤል፣ ላፍቶ ሞልን አለፍ ብሎ በሚገኘው ሚካኤል ጸጋዬ ክሬቲቭ ስቱዲዮ ነው፡፡

## ሙዚቃ

“ባህላችን” የተሰኘ አዲስ የሙዚቃ ስራ ለአድማጭ ተመልካች ሊደርስ ነው፡፡ የመላኩ ሲሳይ (ኢንጅነር) ስራ የሆነው ይህ ሙዚቃ ከሰሞኑ ይፋ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡ የዘፈኑ ግጥምና ዜማ የራሱ የመላኩ ሲሳይ ሲሆን ዜማው ደግሞ በእዮኤል መሀሪ ተሰርቷል፡፡ ዘፈኑ ከሰሞኑ በናሆም ሪከርድስ አማካኝነት እንደሚለቀቅም ተሰምቷል፡፡

ውድ አንባቢዎቻችን ሳምንታዊ የቁጥር ጨዋታ በበዓል ስራዎች ምክንያት አለማካተታችን ከታላቅ አክብሮት ጋር ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

# ማስታወቂያ

በፓየስ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 04 ሳይት አያት 2 ሳይት 4 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000061000300238O0425 የሆነ የይዞታ ማህደር ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለው /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 /ሰላሳ/ ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ማህደር ተደራጅቶ ሰርተፍኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ወ/ሮ አስናቀች መኮንን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የካርታ ቁጥር ቦሌ15/257/14-714/00 ሴሪ ቁጥር 030031 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

አቶ አቤል ሰይፉ ወንድአፍራሽ በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር R-FO-B02 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100400105010702 በሴሪ ቁጥር L 0216986 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግበው የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግንቸዋለው /ይዤዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፍኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ አስካለ ከልክሌ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ--- ወይም በቀድሞው ወረዳ --- ቀበሌ--- የቤት ቁጥር 443 የካርታ ቁጥር 60/5711/01/5738 ሴሪ ቁጥር 105875 በጽ/ቤታችን ያለው ማህደር ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 30 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር አዲስ እና አብርሀም ሀይሌ ገብረዋህድ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ባለቤትነት የይዞታ መለያ ቁጥሩ AA000051308531 ሴሪ ቁጥር 059011 የተሰጠበት ቀን 11/12/2010 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቀን 18/10/2016ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ በአመልካች ጥያቄ መሰረት የይዞታ ካርታ መጥፋቱን በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋዜጣ ታትሞ እና አገኘው የሚል በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ እንዲወጣላቸው እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአቻምየለስ እንዳለ ስም የተመዘገበ ይዞታ በካርታ ቁጥር የካ/210375/2010 የተሰጠበት ቀን 21/10/2010 ዓ/ም የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/የጣ ፖስ/ስቀ/5/11933/ በቀን 25/07/2018 ዓ/ም የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ በመሆኑ ካርታውን አግንቸዋለሁ ወይም መብት አለኝ የሚል አካል ካለ በ90 ቀናት ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው መስሪያ ቤት ማለትም የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ሳይሆን ቢቀር በምትኩ ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የምንሰጠው መሆኑን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ትንሣኤ በትናንት ገጾች

በአብርሃም ገብሬ

ዛሬ ላይ በጋዜጦችና መጽሔት ገጾች ላይ የሚሰፍሩ የበዓላት ዘገባዎችና ኩነቶች፣ የጊዜን መጋረጃ ቀድደው በመሻገር የዘመኑን ሁኔታ ያሳያሉ፡፡ የህትመት ውጤቶቹ የዘመኑን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና የአኗኗር ዘይቤ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ የታሪክ ዘጋቢ ጭምር ናቸው፡፡ ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ፣ በዘመኑ የነበረውን መንፈስና ነባራዊ እውነታ ምን ይመስል እንደነበር ለታሪክ ተመራማሪዎችም ሆነ ያለፈውን ዘመን ለሚመረምሩ ግለሰቦች እንደ ትልቅ የመረጃ ምንጭ ያገለግላሉ። የጋዜጣና መጽሔት ህትመት ዋነኛ ፋይዳውም ይኸው ነው፤ የዛሬን ክስተት ሰንዶ ለነገው የታሪክ ማህደርነት አሻግሮ ማቆየት።

ይህንኑ መነሻ በማድረግ፣ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል የዘመናትን የጊዜ ሰሌዳ ወደ ኋላ በማሽከርከር የቀደሙ የትንሳኤ በዓላትን ድባብ ዳስሷል። የበዓሉ ዋዜማ ዝግጅት፣ የዕለቱ የበዓል እንቅስቃሴና የበዓሉ ማግስት ትውስታ ምን ይመስል እንደነበር ለማሳየትም በኢትዮጵያ የህትመት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸውን የ‘ብርሃንና ሰላም’ ጋዜጣን፣ ‘መነን’ እና ‘Addis Reporter’ መጽሔቶችን ቃኝቷል። እነሆ በቀድሞ የህትመት ውጤቶች ለንባብ የበቁ የበዓል ትውስታዎች በሚከተለው መልኩ አሰናድተነዋል። ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ቤተሰቦች ከቀድሞ ጋዜጣና መጽሔቶች ያገኘናቸው ዘገባዎች የዘመኑን ሁኔታ በሚገባ ስለሚያሳዩ፣ በዘመኑ በተጻፈበት የቋንቋና የአጻጻፍ ዘይቤ እንዳለ ለማውጣት ጥረት አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ!

## የትንሳኤ በዓል በቀደመው ዘመን

የትንሳኤ በዓል ድምቀትና ትርጉም የሚመነጨው አማኙ ለሁለት ወራት ያህል ከሚያደርገው ጾምና ጸሎት (ዐቢይ ጾም) ጋር ተያይዞ ነው። በዚህ የጾምና የጸሎት ወቅት ሕዝበ ክርስቲያኑ የፈጣሪውን ሕማማትና መከራ በጾም እያሰበ፣ በታላቅ ተመስጦ ወደ ልቦናው ይጓዛል። እነዚህ ለሳምንታት የሚዘልቁ የጸሎትና የሱባኤ ጊዜያትም ማሳረጊያቸው የትንሳኤ በዓል ይሆናል። በመሆኑም ስለ ፋሲካ ስናወሳ፣ ለበዓሉ መገኘት መሠረት የሆነውን የዐቢይ ጾምን መንፈሳዊ ጉዞ አለማስታወስ አይቻልም። ጾሙ ለበዓሉ ድምቀት መንገዱን እንደሚጠርግ ሁሉ፣ ትንሳኤም ለነዚያ የጾምና የጸሎት ቀናት የደስታና የብርሃን ምላሽ ሆኖ ይመጣል። ስለሆነም የቀደሙ የሕትመት ውጤቶች ስለ በዓሉ አከባበር ሲዘግቡ፣ የጾሙንና የጸሎቱን ድባብ ከበዓሉ ሁኔታ ጋር አስተሳስረው ቃኝተዋል፡፡

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት፣ በእቴጌ መነን ስም የተሰየመችውና ከኢትዮጵያ ቀደምት ህትመቶች መካከል አንዷ የሆነችው “መነን” መጽሔት፣ ስለ ትንሳኤ ሰፊ ሐተታ ባስነበበችበት በሚያዝያ ወር 1951 ዓ.ም ዕትሟ ጾሙን የሚያወሳ አንድ መጣጥፍ አስነብባለች፡፡ የመጣጥፉ ርዕስ “የነፍስ መሰላል ጾም” ይሰኛል። “ጾም ለነፍስም ሆነ ለሥጋ ብርቱ ተጠቃሚነት ያለው የተፈተነ መድኃኒት ለመሆኑ የሚያጠራጥር ነገር የለም፡፡ ይህ አሁን… የጾምነው ዐቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ… ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት የጾመው ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የሁላችን ጸላኤ ሠናያት ሰይጣን በትዕቢት፡ በስስት፡ በንፍገት፡ በእነዚህ በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ሊፈታተነው ቀርቦ ከክርስቶስ ፊት ድል ሆኖ ተመልሷል” ስትል የጾሙ ምንነትና አስፈላጊነት መጽሔቷ በስፋት አስነብባለች፡፡




ፎቶ- በአብርሃም ገብሬ

ቀደምት የህትመት ውጤቶች ስለትንሣኤ በዓል ኃይማኖታዊ ትርጉም እና ማህበራዊ ፋይዳ የሚያስገነዝቡ የይዘት ሥራዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ አድርገዋል

> “በሚያዝያ 20 ቀን ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ሱቁን ዘግተው ሠራተኞች ከወጡ በኋላ የወይዘሮ በለጥሻቸውና የደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ሱቅ ተቃጠለ። የተቃጠለው ዕቃ ሒሳብ እስከ 2 ሺህ ብር ይሆናል።”

በቀደምት የህትመት ውጤቶች በስፋት ባይሆንም በጣም ውስን የሆነ ሽፋን ለትንሳኤ በዓል መስጠታቸውን የአዲስ ልሳን ዝግጅት ለመታዘብ ችሏል። አልፎ አልፎም ቢሆን የትንሳኤን በዓል በሚመለከት ሽፋን ከሰጡ ቀደምት የህትመት ውጤቶች መካከል በስፋት ተነባቢ የነበረው “ብርሃንና ሰላም” ጋዜጣ ይገኝበታል፡፡ ጋዜጣው በሚያዝያ 23 ቀን 1922 ዓ.ም ዕትሙ፣ “የስቅለትና የትንሳኤ በዓል በግሪክ ቤተ ክርስቲያን” በሚል ርዕስ የሚከተለውን ዘገባ አስነብቧል፤ “የአክሱም ጳጳስ ፓትርያርክ ኒኮላ ቀድሞ እዚህ የነበሩት አሁን ደግሞ እንደገና ወደ አዲስ አበባ መጥተው ዓርብ በሦስት ሰዓት በዓለ ስቅለትን ለማክበር ግሪካውያንም ሁሉ በቤተ ክርስቲያናቸው ተሰብስበው መብራት አብርተው ዑደት አደረጉ፡፡ ፓትርያርክ ኒኮላስም ስለ ኢትዮጵያና ስለ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ፣ ስለ ልዕልት ወይዘሮ መነንና ስለ መኳንንቱ፣ ስለ ሕዝቡ ሁሉ ጸሎት አደረጉ፡፡ በበዓለ ትንሳኤም እንደዚሁ በከተማ ያሉ ግሪካውያን ሁሉ ተሰብስበው ፓትርያርክ ኒኮላስ ቀድሰው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ተናገሩና ሕዝቡን ደስ አሰኝተው አሰናበቱት” ሲል አስነብቧል፡፡

በዚሁ ዕትም ላይ በትንሳኤ በዓል ማግስት የእሳት አደጋ ተከስቷል። በጋዜጣው አደጋውን በሚመለከት እንዲህ ሰፍሯል፤ “በሚያዝያ 20 ቀን ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ሱቁን ዘግተው ሠራተኞች ከወጡ በኋላ ሙሴ ኮርስቶና፡ ሙሴ ጆርጂ ካሉ ጆርጥሎስ ወንድማማቾቹ የሚነግዱበት የወይዘሮ በለጥሻቸውና የደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ሱቅ ተቃጠለ። የተቃጠለው ዕቃ ሒሳብ እስከ 2 ሺህ ብር ይሆናል፡፡ ትጉሁ ከንቲባ ነሲቡ ዘበኛውን በጥሩምባ አስነስተው ከእሳት ያዳኑት ዕቃ 2 ሺህ ብር ይገመታል። ሲቢርቶ የነበረበት ጓዳ እንዳይቃጠል በጎረቤት የነበሩ ዘበኞች ውኃ እየቀዱ በብርታት ባያጠፉት በተራው ያለ ሱቅ ሁሉ አይተርፍም ነበር።… ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴም እጅግ አዝነውላቸው የተቃጠለውን ሱቅ አይተው አይዟችሁ ብለው ተስፋ ሰጥተዋቸዋል…” በማለት ትንሳኤን ከእሳት አደጋ ክስተት ጋር በማስተሳሰር በጋዜጣው ሽፋን አግኝቷል፡፡ ሌላው ትንሳኤን መነሻ አድርገው የተለያዩ መጣጥፎች ካስነበቡ ቀደምት የህትመት ውጤቶች መካከል አንዱ በጊዜው ተነባቢ የነበረው “Addis Reporter” መጽሔት ነው፡፡ በፈረንጆቹ በሚያዝያ 11 1969 “Easter in Ethiopia” በሚል ርዕስ ስለ ዐቢይ ጾም፣ ትንሳኤና በትንሳኤ በዓል ስለሚደረጉ መሰናዶዎች ጥልቅ ዳሰሳ አድርጓል፡፡ በመጣጥፉ መጀመሪያ ላይ ሰፊ ትኩረት የተሰጠው ኢትዮጵያ ለዘመናት ጠብቃ ያኖረችው ኃይማኖታዊ ትውፊትና በዓሉን ለማክበር መነሻ የሆነው ዐቢይ ጾም ጉዳይ ነው። በዓሉ ለዘመናት የቆዩና በቀላሉ የማይሸረሸሩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች መገለጫ መሆኑን በመጥቀስ፣ በተለይም ለ56 ቀናት የሚቆየው የእንስሳት ተዋጽኦ አልባ ጾም በበዓሉ ዋዜማ ላይ የሚፈጥረውን ከፍተኛ ጉጉት በመጣጥፉ ትኩረት አግኝቷል። በመጣጥፉ ጾሙ ረዥምና ጥብቅ በመሆኑ ምክንያት በወጣቱና በአዛውንቱ ትውልድ መካከል የሐሳብ ልዩነት እንዳለ ጠቁሞ፣ አብዛኛው ሕዝብ ግን የጾሙን መንፈሳዊና ሞራላዊ እሴት አክብሮ በጾምና በጸሎት እንደሚቆይ በዝርዝር ያስቃኛል።

በተለይ በዚህ መጣጥፍ አንድ ትኩረት የሚስብና ለዛሬው ዘመን እንግዳ የሚመስል አስገራሚ ጉዳይ በመጣጥፉ ተነስቷል፡፡ ይኸውም በወቅቱ የነበረውን ማህበራዊ ሽግግር አመላካች ወይም “የትውልድ ክፍተት” ጉዳይ በበዓል አከባበር ዙሪያ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እያሳረፈ እንዳለ ተዳስሷል፡፡ በመጣጥፉ እንደሰፈረው፣ በ1960ዎቹ አካባቢ የነበሩ አንዳንድ የተማሩ የሚባሉ የዚያ ዘመን ወጣቶች፣ ለ56 ቀናት የሚዘልቀውን የዐቢይ ጾም ሥርዓት “ከባድ ነው” በማለት ማሻሻያ እንዲደረግ እንደሚጠይቁ አስነብቧል፡፡ እነዚህ ወጣቶች የጾሙን ርዝማኔና ጥብቅነት በምክንያታዊነት ለመተንተንና ምናልባትም “ለውጥ ያስፈልጋል” የሚል መንፈስ ለማሳየት ሲሞክሩ፣ በሌላ በኩል የዚያ ዘመን አባቶችና እናቶች ደግሞ ይህን የዘመናት ትውፊትና የእምነቱን ሥርዓት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ማክበር እንደሚገባ አጥብቀው መከራከራቸውንም መጣጥፉ አስነብቧል፡፡

በዚሁ የ“Addis Reporter” መጽሔት ዕትም ላይ በዓሉን አስመልክቶ የሚታየውን ደማቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴም በስፋት ተዳስሷል። ትንሳኤን ለማክበር የሚደረገው ዝግጅት ከገበያ ግርግር ጀምሮ እስከ ቤት ውስጥ የድግስ መሰናዶ እንደሚዘልቅ ያብራራል፡፡ በተለይም በቅዳሜው ዋዜማ የቤት እመቤቶች የዶሮ ወጥ ለመሥራት የሚያደርጉትን ጥረትና ወንዶች የበዓል በሬና በግ ይዘው ወደ ቤት የሚመለሱበትን ትዕይንት በሥዕላዊ መግለጫ ጭምር አስቀምጦ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ እንደ ጠላና ጠጅ ያሉ የሀገር ባህል መጠጦች መዘጋጀታቸው፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም ቢለያይም ቅሉ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደ አቅሙ በደስታና በፍሥሐ በዓሉን እንደሚያከብር መጽሔቱ በዝርዝር አስነብቧል፡፡

ሌላው በሚያዝያ 16 ቀን 1962 ዓ.ም ለንባብ በበቃችው፤ “መነን” መጽሔት የፋሲካ ዋዜማና ዕለትን የሚያስታውሱ የተለያዩ ጽሑፎች ይዛ ወጥታለች፡፡ “ሰም ለበስ” በተሰኘው የመጽሔቷ አምድ ላይ ፋሲካን የሚያስታውስ ወግ በዚህ መልኩ አስተናግዳለች፤ “አንድ ሰው ነበረ፡፡ ፋሲካ በደረሰ ቁጥር ቤቱ ተጋድሞ ያዙኝ፣ ጥለፉኝ እያለ ቤተሰቦቹን ያስቸግራል። ግን ቢያርዱት እንኳን ሐኪም ቤት አይሄድም፡፡ ታዲያ አሁን ባለፈው ፋሲካ ሰሞን እንደልማዱ ተኝቶ ምጥ የያዛት ሴት ይመስል ሲያጓራ የልብ ጓደኛው የሆነ አንድ ሰው ሊጠይቀው መጣ፡፡ የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ከውጭ የመጣው ሰው እየተገረመ…

“አምና፣ ካቻምናም በፋሲካ ሰሞን ታመህ ነበር፡፡ አምልኮት አለብህ ልበል?” አለና ጠየቀው፡፡

“አውቆ በሽተኛው ከአልጋው ቀና ብሎ አጠገባቸው ሌላ ሰው እንደሌለ ካረጋገጠ በኋላ ‘በእውነት የታመምኩ አይምሰልህ’” አለው፡፡

“ታዲያስ?”

“ለወላጆቼ፣ ለአያቶቼ፣ ለአማቶቼና ለጡት አባቴ ያክፋይ የሚሉትን ዕዳ መክፈል ሰልችቶኝ ነው ፋሲካ በደረሰ ቁጥር የምታመመው” አለውና ባለቤቱ ብቅ ስትል ተጋድሞ ያቃስት ጀመር - በማለት ቀልድ አዘል የፋሲካ ወግ ዳስሳለች፡፡

ይህ የቀድሞ የህትመት ውጤቶች ዳሰሳ እንደሚያሳየው፣ የትናንት የህትመት ውጤቶች የታሪክ መስታወት በመሆን የበዓላትን ኃይማኖታዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን፣ የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ የትውልድ ሽግግር ፈተናዎችንና የበዓል ትውፊቶችን በሚገባ ያሳያሉ። ትንሳኤ በትናንት ገጾች ሲቃኝ፣ ከኃይማኖታዊ ሥርዓቱ ጥብቅነት ጀምሮ እስከ ማህበራዊ መስተጋብሮችና የቀልድ ወጎች ድረስ ያለው ድባብ፣ ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የማይደበዝዝ እሴት መሆኑን ያረጋግጣል። በመሆኑም እነዚህን የታሪክ ማህደሮች መቃኘት፣ ትናንትን በዛሬው መነጽር አይተን የነገውን ባህላዊና ታሪካዊ እሴታችንን እንድንጠብቅ ትልቅ ትምህርት ይለግሰናል፡፡ መልካም የትንሳኤ በዓል ይሁንላችሁ!


1990
GIFT
REAL ESTATE
GIFT REAL ESTATE
መኖር በጊፍት መንደር!
እንኳን ለትንሳኤ በዓል
አደረሳችሁ
htpps.www.giftrealestate.com.et


Fine
Water
ለመላው የክርስትና ዕምነት ተከታዮች
በሙሉ እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ
እያልን በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆንላችሁ
መልካም ምኞታችንን! እንገልጻለን!
መልካም በዓል!
ፋይን ውሃ




# የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ምንድነው፤ እንዴትስ መቅረብ አለበት?

አገልግሎት ማለት እውቀትን ወይም ሙያን መሰረት በማድረግ የተገልጋዮችን ፍላጎት ለማሟላት የሚደረግ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ወይም ጥረት ነው። በሌላ አገላለጽ አገልግሎት የተገልጋዮችን ፍላጎት የማሟላት ሂደት ሲሆን፣ ይህም ሂደት የተገልጋዮችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ዓላማ ተኮር ተግባራትን ያካትታል። እነዚህ ተግባራት ትህትና በተሞላበት መልኩ፣ ስኬታማና ኢኮኖሚያዊ ቅልጥፍና ባለው መንገድ መከናወን ይኖርባቸዋል። የአገልግሎት ውጤታማነትም በጊዜ፣ በመጠን፣ በወጭና በጥራት እንዲሁም በተገልጋይ እርካታ ሊለካ የሚችል ሲሆን፣ በአገልግሎት ተቀባዩ ዘንድ ፋይዳ ያለው እሴት የሚጨምር ተግባር ነው።

## የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ምንነት

የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ማለት የመንግስት ተቋማት የዜጎችን ሁለንተናዊ ፍላጎቶች ለማርካትና የጋራ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚፈጽሙት ስልታዊ፣ ተቋማዊና ህጋዊ ግዴታ ሲሆን፤ ይህ ተግባር ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን፣ አካታችነትን እና ፍትሃዊነትን መሰረት በማድረግ የሚከናወን የተቀናጀ የግብዓትና የሂደት ውጤት ሆኖ ይገለጻል።

የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት አገልግሎት ሰጪው አካል በተቀመጡ የጥራት ደረጃዎችና መለኪያዎች መሰረት ውጤታማና ቀልጣፋ አሰራርን የሚከተልበት መድረክ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ አላስፈላጊ ቢሮክራሲን በማስቀረትና የዜጎችን ንቁ ተሳትፎ በማረጋገጥ በሉዓላዊው ህዝብና በመንግስት መካከል ያለውን ማህበራዊ ውል በተግባር መተርጎም ይቻላል። ስለሆነም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት የመንግስት ተቋማዊ ብቃት መገለጫ ብቻ ሳይሆን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና የሀገር አቀፍ የልማት ግቦች ስኬት ዋነኛ ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

አገልግሎት አሰጣጥ የራሱ መሰረታዊ ባህሪያትና መለኪያዎች ያሉት ሲሆን፣ በዋናነት የተገልጋዮችን ፍላጎት ለማርካት ሰበል በአገልግሎት አቅራቢ ተቋማት የሚፈፀም ተግባር ነው። እነዚህን መሰረታዊ ባህሪያት ጠንቅቆ ማወቅ ለአንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋም በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታትና ውጤታማ አገልግሎት ለማቅረብ ወሳኝ ጠቀሜታ አለው።

## የአገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ ባህሪያት

አገልግሎት ከምርት የሚለይባቸው አምስት ዋና ዋና ባህሪያት አሉት፡-

1. የማይጨበጥና የማይታይ (Intangibility)፡- አገልግሎት ሊታይ፣ ሊዳሰስ፣ ሊሸተት፣ ሊቀመስ ወይም ሊከማች የማይችል ረቂቅ ባህሪ አለው። በዚህም ምክንያት የአገልግሎቱን ጥራትና ትክክለኛ ውጤት አገልግሎት ሰጭው አስቀድሞ ለመተንበይ እንዳይችል ያደርገዋል። አገልግሎት እንደ ምርት ሁሉ ቀድሞ የሚዘጋጅና የሚከማች ሳይሆን በአገልግሎት ሰጭው አካል የሚፈጠርና ለእያንዳንዱ ተገልጋይ በወቅቱ የሚሰጥ ነው። በመሆኑም አገልግሎቱ በተፈለገው መንገድ መሰጠቱን ለማረጋገጥ የተገልጋዩ መኖር፣ አገልግሎቱን መቀበልና በሂደቱ የነበረውን ስሜት መረዳት የግድ ይላል።
2. የማይለያይ (Inseparability)፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት አገልግሎት ሰጪውና አገልግሎት ተቀባዩ ፊት ለፊት ካልተገናኙ አገልግሎት ከአንዱ ወደ ሌላው አይሸጋገርም። አገልግሎት ምንጊዜም ከአገልግሎት ሰጪው ጋር የተቆራኘ ሲሆን አገልግሎቱና አገልግሎት ሰጪው ተቋም ወይም ግለሰብ ሊለያዩ አይችሉም። ስለዚህ የአገልግሎት ጥራት የሚፈጠረውም ሆነ የሚለካው አገልግሎት ሰጪው ወይም እሱን ወክለው አገልግሎቱን በሚሰጡ ሰዎች የስነ-ምግባርና የብቃት ደረጃ ሲሆን፣ ይህም ከተገልጋዩ ፍላጎት ጋር መጣጣም ይኖርበታል።
3. ተለዋዋጭ (Variability)፡- አገልግሎት ልክ እንደ ምርት ሁሉ ተመሳሳይ ጥራት ያለው ነገር በማምረትና አስቀድሞ ጥራቱን በመፈተሽ የሚቀርብ አይደለም። ለተለያዩ ተገልጋዮች የሚቀርበው አገልግሎት በአገልግሎት ሰጪዎች ልምድ፣ ተሞክሮና ባህሪ እንዲሁም በተገልጋዮች አመለካከትና በሌሎች ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች የተነሳ ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። ይህንን ተለዋዋጭ ባህሪ ለመቆጣጠር ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማውጣትና ተከታታይ የሰው ሃይል ማልማት ስራዎችን በማከናወን የተገልጋይ እርካታን ሊያመጣ የሚችል ወጥ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።
4. ለብልሽት ተጋላጭ (Perishability)፡- አገልግሎትን አስቀድሞ አዘጋጅቶ በመደርደሪያ ላይ በማስቀመጥ (በማቆየት) በሌላ ቀን ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አይቻልም። በሌላ አገላለጽ ለዛሬ ያልተጠቀምንበት አገልግሎት ለነገ ሊሸጋገር አይችልም። ይህ ደግሞ ተቋማት አቅርቦትና ፍላጎትን ለማጣጣምና የተገልጋዮችን ፍላጎት ለማርካት እንዳይችሉ እንቅፋት ሊሆንባቸው ይችላል። በመሆኑም በየጊዜው በመልካም ስነ-ምግባርና ስብዕና ማገልገል ሰዋዊ ባህሪ በመሆኑ ይህንን በፍጹም ቅንነት ተቀብሎ መተግበር ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ይጠበቃል።
5. የተገልጋይን ተሳትፎ (Customer Participation) የሚጠይቅ መሆኑ፡- አገልግሎት ያለ ተገልጋይ ተሳትፎ የሚታሰብ አይደለም፤ በአጭሩ ተገልጋይ ከሌለ አገልግሎት የለም። ስለዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች ደንበኞቻቸውን በሂደቱ ውስጥ ማሳተፍ ወይም ወደ እነሱ እንዲመጡ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

**በአቶ ክንፈ ፍቅሬ ከአገልግሎት አሰጣጥና አውትሶርሲንግ ዘርፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የከተማ ግብርና ምርቶች በበዓላት

- **ምርቶቹ በበዓል ወቅት የሚታየውን የገበያ መዛባት ለማስተካከል የላቀ ሚና እየተጫወቱ መሆኑ ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

በአሁኑ ወቅት የዓለም ሕዝብ ቁጥር መጨመርና ፈጣን የከተማነት መስፋፋት የምግብ አቅርቦት ሰንሰለቱን ከፍተኛ ጫና ውስጥ ጥሎታል። ይህንን ተግዳሮት ለመወጣት ደግሞ የከተማ ግብርና እንደ ዘመናዊና ስትራቴጂካዊ መፍትሔ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እየሳበ ይገኛል። የከተማ ግብርና ከጓሮ አትክልት ባለፈ፣ በሕንፃዎች ጣራ፣ በጋራ መሬቶችና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ የእርሻ ዘዴዎችን በመጠቀም ትኩስ የግብርና ምርቶችን ለከተማው ነዋሪ በቅርበት ለማቅረብ የሚያስችል ዘርፍ ነው። ይህ ልምድ የምርት ማጓጓዣ ወጪን ከመቀነሱም በላይ፣ ከተሞች በራሳቸው አቅም የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ እንዲሆኑ እያደረገ ነው።

በዚህ ረገድ ሲንጋፖር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠቀስ መልካም ተሞክሮ አላት። ሀገሪቷ ውስን መሬቷን በአግባቡ ለመጠቀም ባዘጋጀችው '30 በ 30' ዕቅድ እስከ 2030 ዓ.ም ድረስ የከተማዋን የምግብ ፍላጎት 30 በመቶ በሀገር ውስጥ ምርት ለመሸፈን በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የታገዘ የከተማ ግብርናን እያሰፋች ትገኛለች። በተመሳሳይ፣ የፈረንሳይዋ ፓሪስ 'ፓሪስኩልተር' (Parisculteurs) በተሰኘው ፕሮጀክት ከ100 ሄክታር በላይ የሕንፃ ጣራዎችንና ግድግዳዎችን ወደ እርሻ በመቀየር፣ በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠር ቶን አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለነዋሪዎቿ ማቅረብ ችላለች። እነዚህ ከተሞች ግብርናን ከከተማ ውበትና ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በማቀናጀት ለሌሎች ከተሞችም ትልቅ ትምህርት እየሰጡ ነው።

የከተማ ግብርና በምርት አቅርቦት ረገድ ያለው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው። ምርቱ ከአምራቹ በቀጥታ ለሸማቹ ስለሚደርስ የገበያ ዋጋን ከማረጋጋቱም በላይ፣ በረጅም የትራንስፖርት ጉዞ ወቅት የሚባክነውን ምርት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። እንደ ኩባ ዋና ከተማ ሃቫና ያሉ ከተሞችም ከምግብ ፍላጎታቸው ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነውን ትኩስ አትክልት የሚያገኙት ከከተማ ግብርና ነው። ይህ ተሞክሮ እንደ አዲስ አበባ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ከተሞች የኑሮ ውድነትን ለመቀነስና የበዓል ፍጆታን ለማመጣጠን የጀመሩትን "ከሸማችነት ወደ አምራችነት" ጉዞ በሳይንሳዊ መንገድ ለማሳደግና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ተወዳዳሪነት እንዲኖራቸው ለማድረግ እንደ መነሻ የሚወሰድ ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝባዊና ኃይማኖታዊ በዓላት ሲቃረቡ በከተሞች የሚታየው የሸማች ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር የተለመደ ነው። በተለይም የትንሣኤ (የፋሲካ) በዓል የአትክልቶች፣ ሰብሎች፣ የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ፍላጎት ሰማይ የሚነካበት ወቅት በመሆኑ፣ አቅርቦትንና ፍላጎትን ለማመጣጠን መንግሥታዊና ግለሰባዊ ጥረቶች ይደረጋሉ።





ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ለዘንድሮው የትንሳኤ በዓል ወደ ገበያ ከቀረቡ የከተማ ግብርና ምርቶች ጥቂቶቹ

በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ያለው የገበያ ዋጋ ንረትና የአቅርቦት እጥረት ችግርን ለመቅረፍ የከተማ ግብርና አንዱ አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል። በከተማዋ በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች ምርቶቻቸውን ለገበያ በማቅረብ፣ ሸማቹ ማኅበረሰብ ካለበት የኑሮ ውድነት ጫና እንዲያርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

የዘንድሮውን የትንሣኤ በዓል ምክንያት በማድረግ በየካ፣ በቂርቆስ፣ በኮልፌ ቀራኒዮና በሌሎችም ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የከተማ አርሶ አደሮችና ኢንተርፕራይዞች ሰፊ ዝግጅት አድርገዋል። እነዚህ አምራቾች በክላስተርና በግለሰብ ደረጃ ተደራጅተው የዶሮ፣ የእንቁላል፣ የቁም እንስሳትና የወተት ተዋጽኦ ምርቶችን ለሸማቹ እያቀረቡ ነው።

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ንብ እርባታ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በዶሮ እርባታ የተሰማሩት አቶ ዳዊት ሊሻን፣ የከተማ ግብርና ለበዓል ገበያ ማረጋጋት ያለውን ሚና በተግባር እያሳዩ ካሉ አምራቾች መካከል አንዱ ናቸው። አቶ ዳዊትና መሰል አምራቾች በክላስተር ተደራጅተው መሥራታቸው ለምርታማነት መጨመር ትልቅ ፋይዳ አለው።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፣ ለዘንድሮው የትንሣኤ በዓል በግለሰብ ደረጃ 5 ሺህ እንቁላልና 4 ሺህ የሥጋ ዶሮዎችን ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል። በተጨማሪም እሳቸው የሚገኙበት ክላስተር በአጠቃላይ 50 ሺህ እንቁላልና በርካታ የሥጋ ዶሮዎችን በባዛር ላይ በማቅረብ ለነዋሪው ለመሸጥ ተዘጋጅተዋል፡፡

የከተማ ግብርና ከራስ ፍጆታ አልፎ ለገበያ በመትረፉ የኑሮ ውድነቱን ለመቋቋም ትልቅ መሣሪያ መሆኑን አምራቹ ገልጸዋል። በመንግሥት በኩል የሚደረገው የግብዓት አቅርቦትና የባለሙያ ምክር ድጋፍ፣ አርሶ አደሩና የከተማ ግብርና ተሳታፊው በልበ ሙሉነት እንዲያመርትና ውጤታማ እንዲሆን ማድረጉም ተመላክቷል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማም ተመሳሳይ የዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል። የክፍለ ከተማው የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት ባወጣው መረጃ መሠረት፣ በባዛሮች ላይ 100 ሺህ እንቁላል፣ 320 ኪሎ ግራም ቅቤ፣ 89 ሊትር ወተትና 380 ኪሎ ግራም አይብ ለሽያጭ ቀርቧል።

ይህ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ክፍለ ከተማ 150 ኪሎ ግራም ማርና 2 ሺህ የሥጋ ዶሮዎች ለበዓሉ ገበያ የቀረቡ ሲሆን፣ ይህም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በየደረጃው የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎችም የምርቱን ጥራትና የሥርጭት ሂደት በቅርበት እየተከታተሉ ነው።

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ደግሞ አቅርቦቱ ይበልጥ ሰፋት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። የወረዳው የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አንድነት ተሾመ እንደገለጹት፣ ለትንሣኤ በዓል 80 ሺህ እንቁላል፣ 3 ሺህ የሥጋ ዶሮዎችና 25 የደለቡ ከብቶች በባዛር ላይ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

በተጨማሪም 127 በጎች እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው ቅቤና አይብ ለነዋሪው እንዲደርስ ዝግጅት ተደርጓል። ለዚህ የሥርጭት ሂደት ስኬታማነትም ስድስት የመሸጫ ሼዶች ተዘጋጅተው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፣ ይህም ሸማቹ ምርቱን በቀላሉና ያለ ደላላ ጣልቃ ገብነት እንዲያገኝ ይረዳዋል።

የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማም በበዓል አቅርቦት ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው። በክፍለ ከተማው የእንስሳት ልማት ቡድን መሪ አቶ ሀብታሙ ቃበታ እንደገለጹት፣ ለትንሣኤ በዓል 950 ሺህ እንቁላልና 45 ሺህ የሥጋ ዶሮዎችን ለማቅረብ ታቅዶ ሰፊ ሥራ ተከናውኗል።

እስካሁንም 520 ሺህ እንቁላል፣ 22 ሺህ የሥጋ ዶሮ፣ 32 ሺህ በግና 4 ሺህ 500 በሬዎች በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ለገበያ ቀርበዋል። ይህ አኃዝ የሚያሳየው የከተማ ግብርና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱንና የከተማዋን ነዋሪዎች የምግብ ፍላጎት የመሸፈን አቅሙ እየጎለበተ መሆኑን ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶክተር ደጀኔ ጌታቸው ለዘንድሮው የትንሣኤ በዓል ከ10 ሚሊዮን በላይ እንቁላል፣ 81 ሺህ በላይ በግ እና ፍየል ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር ከ400 ሺህ በላይ ዶሮዎች (160 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ) እና 1 ሺህ 560 የደለቡ በሬዎች መዘጋጀታቸውን ዶክተር ደጀኔ አረጋግጠዋል። በየቀኑ የሚቀርበው 419 ሺህ ሊትር ወተት ደግሞ በከተማዋ ያለውን የወተት ምርት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያረጋጋው ይጠበቃል።

የከተማ ግብርናው ከእንስሳት ውጤቶች ባለፈ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍም ውጤታማ መሆኑ ታይቷል። ለበዓሉ 20 ሺህ 367 ቶን የሚጠጋ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጎመንና ሌሎች አትክልቶች እንዲሁም 9 ሺህ 60 ኪሎ ግራም የማር ምርት መቅረቡ የገበያ መረጋጋቱን ያጠናክረዋል።

ኮሚሽኑ ምርቶቹን ለሸማቹ የሚያቀርብበት ዋጋም ተመጣጣኝ ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በአምራቾች መሸጫ ሱቆች አንድ እንቁላል በ14 ብር ሂሳብ እየቀረበ ይገኛል። ይህ ዋጋ ከወትሮው የገበያ ዋጋ በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ፣ የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።

የሥርጭት ሂደቱንም ለማቀላጠፍ በከተማዋ በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች 163 የሰንበት ገበያዎችና በርካታ ባዛሮች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ የገበያ ስፍራዎች አምራቾችንና ሸማቾችን በቀጥታ የሚያገናኙ በመሆናቸው፣ በደላላ ምክንያት የሚፈጠርን የዋጋ ጭማሪ ያስቀራሉ።

የመንግሥት ዋነኛ ዓላማ ማኅበረሰቡን ከሸማችነት ወደ አምራችነት ማሸጋገር ነው። ከለውጡ በፊት 150 ሺህ ብቻ የነበረው የከተማ ግብርና ቤተሰብ፣ አሁን ላይ በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ታግዞ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን መድረሱ የዘርፉን ስኬታማነት ያበስራል።

የእንስሳት ልማትና ልኅቀት ማዕከልም እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ አቅርቦቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል። ማዕከሉ ከመደበኛ ግብይት ባለፈ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የምርት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የአቅርቦት ሥራ እየሠራ ይገኛል። የከተማ ግብርና ምርቶች በበዓል ወቅት የሚታየውን የገበያ መዛባት ለማስተካከል የላቀ ሚና እየተጫወቱ ነው። ማኅበረሰቡ በእነዚህ የሰንበት ገበያዎችና ባዛሮች በመጠቀም፣ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ የቀረበው ጥሪም ወቅታዊና አስፈላጊ ነው።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ተቋማዊ ኃላፊነትና ብሔራዊ ኩራት የተቆራኙበት፡- “አዲስ መሶብ”

**በደረጀ ታደሰ**

በማንኛውም ሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር የሉዓላዊነት፣ የማንነትና የአንድነት ተምሳሌቶች ናቸው። በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት እና በሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 (እንደተሻሻለው) መሠረት እነዚህ ምልክቶች ልዩ ጥበቃና ክብር ይደረግላቸዋል። በተለይም የመንግሥት ተቋማት እነዚህን እሴቶች የማክበር፣ የማስከበር፣ የማዘመር እና ለዜጎች ምሳሌ የመሆን ቀዳሚ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የትምህርት ተቋማት እና የጸጥታ አካላት ሰንደቅ ዓላማን የመስቀልና ብሔራዊ መዝሙር የማዘመር ተግባርን እንደ መደበኛ የሥራ አካል ሊመለከቱት ይገባል። ሕጉ እንደሚደነግገው፣ ሰንደቅ ዓላማው በየቀኑ በጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ተሰቅሎ ማታ በ12፡00 ሰዓት መውረድ አለበት። ይህ ተግባር የሚከናወነው በሕግ አስገዳጅ ስለሆነ ብቻ አይደለም፤ ተግባሩ በትውልዱ ውስጥ የሀገርን ክብር እና ፍቅር የማሳወቅ፣ የማስረፅ፣ ይህንንም በተሰማሩበት የሥራ መስክ ለመግለጥ ዝግጁ የመሆን ትርጉም አለው። በተለይም በትምህርት ተቋማት በጠዋት ሰልፍ ላይ የሚከናወነው የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ-ሥርዓት አዳጊዎች ስለ ሀገራቸው ፍቅርና ክብር ያላቸውን መረዳት የበለጠ ያሳድገዋል።

የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ጉዳይን እዚህ ላይ ያነሳነው በምክንያት ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ “ተአምራዊ ለውጥ” እያመጣ በሚገኘው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት፤ እየተተገበረ ያለን ተጨማሪ አዲስ በጎ ልምድ ለመዳሰስ እንጂ።

የአዲስ መሶብ ተቋማዊ ሁኔታ በብዙ መመዘኛ፣ ከሌሎች መሰል ተቋማት “አዲስነቱ” በልዩነት ጎልቶ ይታያል። የተቋሙ ሕንጻዎች ውጫዊና ውስጣዊ ገጽታ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አደረጃጀትና አጠቃቀም፣ የሥራ ሥነ ምግባሩ የተጠበቀ ብቃት ያለው የሰው ኃይል፣ የአሠራር ሥርዓቱ … በአርአያነት እንዲጠቀስ አድርጎታል። ዓመት ባልሞላው ዕድሜ ውስጥ “አዲስ መሶብ” የሚለው ስም በብዙዎች አእምሮ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ በቴክኖሎጂና በብዙ ሙያተኞች የተደገፈ፣ የተገልጋይን እርካታ ከፍ ያደረገ የመንግሥት አገልግሎት የሚሰጥበት ምቹና ውብ ተቋም እንዲከሰት በማስቻል ላይ ይገኛል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ የሀገር እና የሕዝብ ፍቅር እና ክብር ከሚገለጥባቸው የጋራ እሴቶች መካከል የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓት በወጉ የሚከናወንበት ተቋም መሆኑ፤



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የማውጣት ሥነ ሥርዓት ሲካሄድ

አዲስ መሶብን ከማለዳው ፈክቶና ደምቆ ከሩቅ እንዲታይ አቅም ሆኖታል። እኛም ይህንን መነሻ በማድረግ የአዲስ መሶብ ሠራተኞችና አመራሮች የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን የሚያከናውኑበትን አግባብ ለመዳሰስ ሞክረናል።

አቶ ቴዎድሮስ ማስረሻ፣ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ ናቸው። እሳቸው እንደሚገልጹት፤ በአዲስ መሶብ እውን እንዲሆኑ ከተያዙ ቁልፍ ዓላማዎች መካከል፡- የተሟላ ተቋማዊ ግንባታ አንዱ ነው። ለዚህ ዓላማ ስኬት ከሚያግዙ ወሳኝ አቅሞች መካከል የተቋሙን የአሠራር መርህና የሥራ ሥነ ምግባርን ጠብቆ ማገልገል የሚችል የሰው ኃይል መፍጠር ነው። ይህንንም መነሻ በማድረግ በተቋሙ የሚከናወኑ የሰው ኃይል ቅጥርና ስምሪት ተግባራት በጥብቅ ዲሲፕሊን ይመራሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ማንኛውም የተቋሙ ሠራተኛ ወደ ተቋሙ ተቀላቅሎ በይፋ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሚወስዳቸው መሠረታዊ ሥልጠናዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል የሥራ ሥነ ምግባርን የተመለከተው አንዱ ነው። ሠራተኛው ከፀጉር አቆራረጥ ጀምሮ፣ የሥራ ላይ አልባሳትን (የደንብ ልብስን)፣ የተገልጋይን አክብሮትና መስተንግዶ፣ የሥራ ሰዓትን በሥራ ላይ ማዋልና በመሳሰሉት የተቋሙ የሥራ መርህ ላይ ሥልጠና ከወሰደ በኋላ፤ የሥራ መርህን አክብሮ ለማገልገል በፊርማው ያረጋግጣል። ይህን አሠራር በመከተል ነው ሠራተኞች በሥራ ላይ የሚገኙት። አዳዲስ ወደ ተቋሙ የሚገቡ ሠራተኞችም በዚሁ መስመር የሚያልፉ ይሆናል፤ ምክንያቱም የተቋም ግንባታው አንድ አካል ስለሆነ።

የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን የማከናወን ልምድ፤ የታለመውን ጠንካራ እና ትውልድ ተሻጋሪ ተቋማዊ ግንባታ ሂደት ለማሳካት የሚያግዝ እሴት ተደርጎ በተቋሙ እየተተገበረ መሆኑን አቶ ቴዎድሮስ አንስተዋል። እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሕዝብ መዝሙርን በመዘመር የሰንደቅ ዓላማ ማውጣት ሥነ ሥርዓት እየተተገበረ ይገኛል። በየሳምንቱ ሰኞ ጠዋት በሚከናወነው የሰንደቅ ዓላማ የማውጣትና ብሔራዊ የሕዝብ መዝሙር የመዘመር ሥነ ሥርዓት ላይ ሁሉም የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች በቅጥር ግቢው ውስጥ በመገኘት በታላቅ ሀገራዊ ፍቅር ይፈጽማሉ። ይህ ሁነት የሀገር ፍቅርን በማስረፅ፣ ይህን የተሰጠን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት፣ አገልጋይነት ለሕዝብና ለሀገር የሚሰጥ አንዱ የክብር መገለጫ መሆኑን በመረዳት፣ በተግባር እንዲገልጹት እያገዘ ይገኛል።

የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን ማከናወን ከተቋም የተሻገረ ፋይዳ እንዳለው የአዲስ መሶብ ሠራተኞችም ይመሰክራሉ። ወጣት የአብስራ አበበ በአዲስ መሶብ ዋና መሥሪያ ቤት የፋይናንስ ባለሙያ ነው። እሱ እንደሚናገረው፤ በሳምንት አንድ ቀን፣ በዕለተ ሰኞ፣ ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ላይ የሚካሄደውን የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን በጉጉትና በናፍቆት ነው የሚጠብቀው። መርሃ ግብሩ የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች በተገኙበት በታላቅ ድምቀትና ክብር ይከናወናል።

የከፍተኛ ትምህርቱን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያጠናቀቀውና የሥራ ዓለምን በአዲስ መሶብ ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀላቀለው የአብስራ፤ የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን ማክበር ያቆመው የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ እንደሆነ ያስታውሳል። ከዚያ በኋላ ይህንን ሥነ ሥርዓት በአዲስ መሶብ የሚያከብርበት ሁኔታ መፈጠሩ እና ተቋማዊ ልምድ መሆኑ፣ ለሠራተኛውና ለተገልጋዩ ማኅበረሰብ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይናገራል። ይህንን በተመለከተ፤ “የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓት በተቋሙ መከናወኑ ሠራተኛውና አመራሩ የሀገር ፍቅር ስሜቱ ከፍ እንዲል ያስችላል። ሕዝብን በቅንነት፣ በታማኝነትና በብቃት የማገልገል ስሜትን ያሳድጋል:: የሞራል ልዕልናን በማሻሻል ከብልሹ አሠራር ይጠብቃል:: እርስ በእርስ የመቀራረብን አጋጣሚ ይፈጥራል:: ለተገልጋዩ ማኅበረሰብ ምሳሌና ተአማኝ ለመሆን ያስችላል” በማለት ያስረዳል::

በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትልቁ ስብራት የነበረውን የብልሹ አሠራር መስፋፋት፣ ያልተገባ የተገልጋይ እንግልትና ስቃይ መሆኑን የጠቆሙት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊው፤ ችግሮቹን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቅረፍ እንደ ተቋም በመደበኛነት እየተከናወነ ያለው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓት በሠራተኞች የሥራ መንፈስና የሀገር ፍቅር ስሜት ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ በመፍጠር የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ሥራ ወዳድነትን፣ አንድነትን፣ የተቋም ባለቤትነትን የመሳሰሉ በጎ እሴቶች በሠራተኞች እንዲሰርፅ በብሔራዊ መዝሙር የታጀበ የሰንደቅ ዓላማ ማውጣት ሥነ ሥርዓት አበርክቶው የጎላ ነው ብለዋል።

በተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ ሲተገበር የቆየው ይህ ልምድ፤ በቅርቡ ለአገልግሎት በበቁት ቅርንጫፎችም በታላቅ ዲሲፕሊን መተግበሩን ቀጥሏል።


የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን የሚገባውን ክብር ሰጥቶ በቋሚነት የማከናወኑ ልምድ በብዙ ተቋማት ዘንድ ጉድለት ያለው የመሆኑ ጉዳይ በገሃድ የሚታይ መራር እውነት ነው። ይህም ሆኖ፤ በዘመናት ተቋማዊ ሂደት ውስጥ ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር የሚገባውን ክብር እንደሰጡ የዘለቁ ተቋማት አሉ። በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱ መካከል የኢትዮጵያ አየር መንገድ (Ethiopian Airlines) አንዱ ሲሆን፤ ልምዱም ለሌሎች ተቋማት ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው። አየር መንገዱ ሰንደቅ ዓላማውን በዓለም ዙሪያ በሚገኙ አውሮፕላኖቹ ላይ በክብር ከመሸከሙ ባለፈ፣ በበረራ አካዳሚው (Aviation Academy) ውስጥ ለሥነ-ሥርዓቱ የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ነው።

ወደ ተቋሙ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ሠራተኞችን አስቀድሞ መሠረታዊ ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ የሚያደርገው ተቋሙ፣ ሥልጠናዎቹ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ አካዳሚ (Aviation Academy) እንዲሰጡ ማድረጉ፤ የሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ሥነ ሥርዓትን በሥራ ቦታ እንዲተገብረው እንዲሁም ልምድ አድርጎ እንዲይዘው የአየር መንገዱ የዳበረ ልምድ በተሞክሮነት ጠቅሞታል። በመሆኑም፤ በርካታ የመንግሥት ተቋማትን በአንድ ጥላ ሥር ባቀፈው የአዲስ መሶብ፣ በጋራ የሚከናወነው የሰንደቅ ዓላማ እና የመዝሙር ሥነ-ሥርዓት “አንድ ማዕከል” የሚለውን ስያሜ ወደ ተግባራዊ አንድነት ለመቀየር ትልቅ ዕድልና አቅም ይፈጥራል። በተጨማሪም በዲጂታል መድረኮቹ ላይ የሀገርን ምልክቶች በክብር በማስቀመጥና በተግባር በመግለጥ፣ ዜጎች የመንግሥት አገልግሎት እያገኙ መሆኑን እንዲተማመኑ ያደርጋል።

በአጠቃላይ የሰንደቅ ዓላማና የብሔራዊ መዝሙር ሥነ-ሥርዓቶች የመንግሥት ተቋማት መገለጫዎች ናቸው። ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እስከ አዲስ መሶብ ዲጂታል አገልግሎት ያሉት ልምዶች እንደሚያሳዩት፣ እነዚህን እሴቶች ማክበርና ማስከበር የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው። ተቋማትም ሆኑ ዜጎች ለሀገራዊ ምልክቶች የሚገባቸውን ክብር በመስጠት ሉዓላዊነትና አንድነት ጸንቶ እንዲዘልቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የጨቅላ ህፃናትን ሕይወት እየፈተነ ያለው የጤና እክል




ፎቶ- ከገፀ ድር

ደም እንዲረጋ የሚያደርጉ የደም ህዋሶች እጥረት የጨቅላ ህፃናት የጤና ስጋት ሆኗል

በሸዋርካብሸ ቦጋለ

ደም እንዲረጋ የሚያደርጉ የደም ህዋሶች (ፕላትሌት) እጥረት በአሁኑ ወቅት የዓለም አቀፍ የጤና ዘርፍ አንገብጋቢ ስጋት ሆኗል። ይህ ችግር በተለይም በታዳጊ ሀገራት፤ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የብዙዎችን የጨቅላ ህፃናት ሕይወት ለከፍተኛ አደጋ እያጋለጠ ይገኛል። የጨቅላ ህፃናት የፕሌትሌት ማነስ (Neonatal Thrombocytopenia) በጨቅላ ህፃን ደም ውስጥ ያለው የፕሌትሌት መጠን ከ150,000/μL (ማይክሮ ሊትር) በታች የሚሆንበት የሕክምና ሁኔታ ነው። ፕሌትሌቶች በደም ውስጥ የሚገኙ ጥቃቅን የሕዋስ ክፍሎች ሲሆኑ፣ የቆሰሉ የደም ሥሮችን በመጠገንና ደም እንዲረጋ በማድረግ ደም መፍሰስን የመከላከል ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ በጨቅላ ህፃናት ላይ ከ 1 በመቶ እስከ 5 በመቶ በሚሆኑ ሰዎች ላይ የሚታይ ቢሆንም፣ በጽኑ ሕሙማን ጨቅላ ህፃናት ክፍል (NICU) ውስጥ በሚገቡ ሕፃናት ላይ ግን መጠኑ በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል፤ ይህም እስከ 25 በመቶ እስከ 50 በመቶ የሚሆኑት ሕፃናት በቆይታቸው ወቅት የፕሌትሌት መጠን መቀነስ ሊያጋጥማቸው ይችላል።

የጨቅላ ህፃናት የደም ችግሮች (Neonatal Hematologic Problems) በመጀመሪያዎቹ 28 ቀናት ውስጥ የሚከሰቱ የደም ክፍሎችን፣ ቀይ የደም ሕዋሳት፣ ነጭ የደም ሕዋሳት፣ ፕሌትሌቶች እና የደም መርጋት ሥርዓትን የሚያጠቁ የተለያዩ መዛባቶችን ያጠቃልላል። ጨቅላ ሕፃናት ፈጣን የፊዚዮሎጂ ለውጥ ስለሚያደርጉ፣ የደማቸው ሁኔታ ከትላልቅ ልጆችና ከአዋቂዎች በእጅጉ የተለየ ነው። የዚህ የጤና ቀውስ ዋነኛ ሰለባዎች ደግሞ የነገ ሀገር ተረካቢ የሆኑ ህፃናት ናቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በጨቅላ ሕፃናት ላይ የሚከሰት የፕሌትሌት ማነስ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የሞት አደጋ (Neonatal Thrombocytopenic Mortality) አሳሳቢ የጤና ችግር ነው። የፕሌትሌት ማነስ በራሱ ብቻ ሳይሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ ከሌሎች ለሕይወት አስጊ ከሆኑ የጤና ችግሮች ጋር ተያይዞ ስለሚከሰት የሞት አደጋን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። ጨቅላ ሕፃናት የፕሌትሌት ማነስን (Neonatal Thrombocytopenia) የሚያባብሱ ሁኔታዎች በሁለት ዋና ዋና የጊዜ ገደቦች ተለይተው የሚታዩ ሲሆን፣ እነዚህም ሕፃኑ ከመወለዱ በፊት እና በኋላ በሚገጥሙ የጤና ችግሮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በመጀመሪያዎቹ 72 ሰዓታት ውስጥ የሚከሰተው የፕሌትሌት ማነስ (Early-onset) አብዛኛውን ጊዜ ከእናት ጤና ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ በተለይም በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት (Preeclampsia)፣ የእንግዴ ልጅ በቂ ምግብና ኦክስጅን ለጽንሱ አለማድረስ (Placental Insufficiency) እና በማህፀን ውስጥ የሕፃኑ እድገት መገታት (IUGR) ዋና ዋናዎቹ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው። በተጨማሪም ሕፃኑ በሚወለድበት ወቅት የሚገጥመው የኦክስጅን እጥረት (Perinatal Asphyxia) እና የእናትየው የሰውነት መከላከያ የሕፃኑን ፕሌትሌት እንደ ባዕድ ነገር አድርጎ የሚያጠቃበት ሁኔታ (NAIT) ለዚህ ችግር መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ከተወለዱ ከ72 ሰዓታት በኋላ የሚከሰተው የፕሌትሌት ማነስ (Late-onset) ደግሞ በዋነኝነት የሚነሳው ከተወለዱ በኋላ በሚመጡ አጣዳፊ የጤና ችግሮች ምክንያት ነው። ለዚህም ዋነኛው እና በጣም አደገኛው መንስኤ የደም መመረዝ ወይም ኢንፌክሽን (neonatal Sepsis)፣ በተጨማሪ በተለይ ያለ ዕድሜያቸው በሚወለዱ ሕፃናት ላይ የሚከሰተው ከባድ የአንጀት ቁስለት (NEC) እና በሰውነት ውስጥ ያለ አግባብ የደም መርጋትና መፍሰስን የሚያስከትለው የዲ.አይ.ሲ (DIC) ሁኔታ የፕሌትሌት መጠንን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳንሳሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ሁኔታዎች በአንድ ላይ ተዳምረው የጨቅላ ሕፃኑን የመከላከል አቅም በማዳከም ለከባድ የፕሌትሌት ማነስና ለሞት አደጋ ሊዳርጉ ስለሚችሉ ፈጣን የሕክምና ክትትል ያስፈልጋቸዋል።

ችግሩ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ በተለያዩ ተመራማሪዎች በተጠኑ ጥናቶች ላይም እንደሚያሳየው በጽኑ ሕሙማን ክፍል ከሚታከሙ ጨቅላ ሕፃናት መካከል ከ26 ነጥብ 02 በመቶ እስከ 66 በመቶ የሚደርሱት ጨቅላ ሕፃናት የፕሌትሌት ማነስ ችግር እንዳለባቸው ያመላክታል። ይህንን መነሻ በማድረግ፤ የዳግማዊ ምኒልክ ህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር የሆኑት መምህር ዮሐንስ ጎዴ ደም እንዲረጋ የሚያደርጉ የደም ህዋሶች (ፕሌትሌት) እጥረት ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት የመዳን እና የመሞቻ ግዜ የሚተነብይ ጥናት አድርገዋል፡፡ ኮሌጁ በ2017 ዓ.ም ለተመራማሮዎቹ በሰጠው እድል አሸናፊ ሆነው ባካሄዱት በዚህ ጥናት 14 ነጥብ 1 በመቶ ደም እንዲረጋ የሚያደርጉ የደም ህዋሶች እጥረት ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት የሞቱ ሲሆን አማካይ የሞት ጊዜ 23 ነጥብ 36 ቀናት መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በተመረጡ የመንግስት ሆስፒታሎች ተኝተው ከሚታከሙ ጨቅላ ህፃናት ውስጥ ደም እንዲረጋ የሚያደርግ ህመም ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት ችግሩ የሚመጣባቸው መች ነው? የሚለውን የሚተነብይ ነው፡፡ ህፃናቶች ህፃናት ክፍል ከገቡ በኋላ ችግሩ የሚመጣው፤ የሚድኑት፤ እንዲሁም የሚሙቱት በስንተኛው ቀን ነው? በ5ኛው? በ10 ወይስ በ15ኛው ቀን ነው? የሚል ሆኖ የፕሌትሌት እጥረት ችግር ከገጠማቸው ቀን እስከ 28ኛው ቀን ድረስ ክትትል በማድረግ ያካተተ ጥናት ነው የተደረገው፡፡

እንደ መምህር ዮሐንስ ማብራሪያ፣ ህፃናት ከተወለዱ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች በጨቅላ ህፃናት ክፍል ውስጥ ይተኛሉ፤ በዚያም ለአንድ ወርና ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜያት የሚቆዩበት አጋጣሚ አለ፡፡ የጨቅላ ህፃናት ክፍል እንዲገቡ/እንዲተኙ ከሚያደርጋቸው ምክንያት ውስጥ ያለግዜ መወለድ፣ ታፍነው የሚወለዱ ህፃናት፤ የኪሎ ማነስ፤ ኢንፌክሽን(neonatal sepsis)፤ የአተነፋፈስ ችግር /በተለይም ያለግዜያቸው የሚወለድ ህፃናት ላይ ሳንባ ሳይጠነክር መወለድ/፤ የሰውነት ቢጫ መሆን የመሳሰሉት ምክንያቾ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መምህር ዮሐንስ በዚህ ጥናታቸው ከእናት ጤና ጋር ተያይዞ በተለይም በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት/preclampsia/ ካለባቸው እናቶች የተወለዱ ሕፃናት፣ በህፃኑ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ባይ ናቸው። እናትየው ላይ የሚከሰተው ከፍተኛ የደም ግፊት በእንግዴ ልጅ (placenta) በኩል የሚደረገውን የደም ዝውውር ስለሚቀንስ፣ ሕፃኑ በማህፀን ውስጥ እያለ በቂ ኦክስጅንና ምግብ አያገኝም። ይህ ሁኔታ የሕፃኑ መቅኒ (bone marrow) ፕሌትሌት የሚያመነጩ ሕዋሳትን (megakaryocytes) እንዳያመርት ተጽዕኖ ያሳድራል።

ሌላኛው የመምህር ዮሐንስ የጥናት ግኝት በጣም ዝቅተኛ የልደት ክብደት (Very Low Birth Weight - VLBW) ሲወለድ ክብደታቸው ከ1500 ግራም (1.5 ኪሎ ግራም) በታች መሆኑ፣ በፕሌትሌት ማነስ ለተጠቁ ሕፃናት የአደጋውን መጠን በሦስት እጥፍ በላይ ይጨምረዋል።

በወሊድ ወቅት የሚከሰት የኦክስጅን እጥረት (Perinatal Asphyxia) በፕሌትሌት ማነስ ለተጠቁ ሕፃናት ህልውና ላይ ያለውን ከፍተኛ ተጽዕኖ በግልጽ ያሳያል። ሕፃኑ በሚወለድበት ቅጽበት በቂ ኦክስጅን ወደ ሰውነቱና ወደ አንጎሉ አለመድረሱ።

ሌላኛው የጥናት ግኝት የአንጀት ቁስለት (Necrotizing Enterocolitis - NEC) በፕሌትሌት ማነስ ለተጠቁ ሕፃናት ላይ የሚያስከትለውን አስከፊ ጉዳት በግልጽ ያሳያል። የአንጀት ቁስለት በተለይ ያለ ዕድሜያቸው በሚወለዱ ሕፃናት ላይ የሚከሰት አደገኛ የጤና ችግር ሲሆን፣ የፕሌትሌት ማነስ ባለበት ሁኔታ የሞት አደጋውን በእጅጉ ያባብሰዋል።

ይህ የመጨረሻው የመምህር ዮሐንስ የጥናት ግኝት ህፃናት እንደተወለዱ የእናት ጡት ወተት ዘግይቶ መጀመርም ተጋላጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች የሚመደብ ሲሆን፣ ህፃናት እንደተወለዱ በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ የእናት ጡት ወተት ማግኘት እንዳለባቸው የጠቆሙት መምህር ዮሐንስ፣ ነገር ግን ህፃኑ/ኗ የጤና ችግሮች ካለባቸው ለምሳሌ፡- ታፍኖ ከተወለድ፤ ያለግዜ መወለድ (በተለይም ከ34 ሳምንት በታች)፣ ከባድ የአንጀት ቁስለት፤ ከፍተኛ የሆነ የአተነፍፈስ ችግር ካለ ወተት ዘግይተው ሊጀምሩ ይችላሉ፤ ስለሆነም እነዚህ ህፃናት በተጓዳኝ የፕሌትሌት እጥረት ሲያጋጥማቸው ያመላክታል፡፡

ከላይ በጥናቱ የተቀመጡ ችግሩን ለመቀነስ እናቶች በእርግዝና ወቅት የሚያደርጉትን ክትትል በማጠናከር የደም ግፊት ምልክቶችን አስቀድሞ መለየትና መቆጣጠር ያስፈልጋል። ከባድ የደም ግፊት ካለባቸው እናቶች ሕፃናት በሚወለዱበት ወቅት፣ ሕፃናቱ የፕሌትሌት ማነስ ሊኖርባቸው እንደሚችል ግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊው የጽኑ ሕሙማን ክትትል (NICU) መደረግ አለበት።

ክብደታቸው አነስተኛ የሆኑ ሕፃናት የበሽታ መከላከል አቅማቸው ደካማ በመሆኑ፣ በሆስፒታል ውስጥ ለሚከሰቱ ኢንፌክሽኖች (Sepsis) እንዳይጋለጡ እጅግ የላቀ የንጽሕና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ይገባል። የደም መመረዝ ከተከሰተ የፕሌትሌት መጠኑን በከፍተኛ ፍጥነት ስለሚያሳንሰው ለሞት ያፋጥናቸዋል። ክብደታቸው አነስተኛ ለሆኑ ሕፃናት ሙቀት መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ የእናትና የሕፃን የገላ ለገላ ንክኪ የሕፃኑን የልብ ትርታና አተነፋፈስ በማረጋጋት የሰውነቱን የደም ዝውውር ሥርዓት ስለሚያጠነክር ባለቡያዎች ለእናቶች ግንዛቤ መስጠት አለባቸው።

የአንጀት ቁስለት (NEC) ለሕፃኑ በተለይም ያለ ዕድሜያቸው ለተወለዱት የእናት ጡት ወተትን መስጠት ለአንጀት ቁስለት (NEC) ዋነኛው መከላከያ ነው። የእናት ወተት አንጀትን የሚያጠናክሩና ጎጂ ባክቴሪያዎችን የሚከላከሉ ንጥረ ነገሮችን ይዟል። ብዙ ጊዜ ሕፃናት ስለታመሙ ብቻ ምግብ እንዲያቆሙ ይደረጋል። ነገር ግን መምህር ዮሐንስ በጥናታቸው እንዳረጋገጡት፣ ያለምክንያት ምግብን ማዘግየት አደጋው የከፋ ስለሆነ፣ የሕክምና ባለሙያዎች ሕፃኑ ምግብ መውሰድ የማይችልበት በቂ የሕክምና ምክንያት (ለምሳሌ የአንጀት መቁሰል፤ ከፍተኛ የአተነፍፈስ ችግር) ከሌለ በስተቀር አመጋገብን ማዘግየት የለባቸውም። በጣም በትንሽ መጠን (Trophic feeding amount) ተጀምሮ የሕፃኑ አንጀት እየለመደ ሲመጣ መጠኑን በሂደት መጨመር (Minimal Enteral Nutrition) እንዳለባቸው መምህር ዮሐንስ ይመክራሉ።

ከጤና ባለሙያዎች በተጨማሪ የጤና ተቋማትም ከደም ባንክ አገልግሎት ጋር በመነጋገር አስፈልጊውን ደም ማሟላት በተለይም ፕሌትሌት፤ ማሟላት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ በመሆኑም ይህንን መናሻ በማድረግም ህብረተሰቡ የደም ልገሳን ማበረታታትና ዘመናዊ የደም ማጣሪያ ማሽኖችን በስፋት ማቅረብ ለነገ የማይባል የሰው ልጅ ህልውና ጉዳይ ሆኗል። ወላጆች በተለይም እናቶች ጨቅላ ህፃናት ሆስፒታል እያሉም ሆነ ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ልዩ ትኩረትና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ በጨቅላ ህፃናት ላይ የአተነፋፈስ ችግር፣ ጡት አለመሳብና መሰል አደገኛ ምልክቶችን ሲመለከቱ በአፋጣኝ ወደ ህክምና ተቋማት መሄድ እንዳለባቸው በዳግማዊ ምኒልክ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የጨቅላ ህፃናት ትምህርት ክፍል መምህር ዮሐንስ ጎዴ ይመክራሉ፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የመዲናዋ ደን ልማትና ጥበቃ ምን ይመስላል?

- ካርታ ሳይኖረውና የራሱ ሳይሆን የመንግስትን ደን የጨፈጨፈ ከፍተኛ ወንጀል እንደፈጸመ ተወስዶ ከፍተኛው የቅጣት ደረጃ ይጣልበታል

**በለይላ መሀመድ**

ከተሜነትና ደን ብዙውን ጊዜ ተቃራኒ ተደርገው ይታያሉ፡፡ ለምን ቢባል ከተሜነት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ደኖች ይመነጠራሉ፡፡ ዛፎች እየተቆረጡ ለቤት መስሪያነት ይውላሉ፡፡ በየጊዜው ወደ ከተሞች የሚፈልሰው ራሱን ለማኖር ሲል ደኖች ላይ ክንዱን ያሳርፋል፡፡ በዚህ ምክንያት ደን ይመናመናል፡፡ አዲስ አበባም የዚህ ችግር ሰለባ ሆና ቆይታ፣ የደን ሀብት ሽፋኗ ተመናምኖ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሶም ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መረጃ እንደሚያሳየው፣ በ2008 ዓ.ም የአዲስ አበባ የደን ሽፋን 2 ነጥብ 8 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ የወንዝ ዳርቻዎቿም በነዋሪዎች ተጨናንቀው እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ይህም ለአካባቢ ብክለት እና ለአየር ንብረት ለውጥ መዛባት ሁነኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው ይታወቃል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

በአዲስ አበባ እንጦጦ አካባቢ ያለው የደን ሀብት ልማት ከፊል ገፅታ

የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል የከተማዋ የደን ሀብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንዳይጨፈጨፍና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አንዱ ነው፡፡ ለመሆኑ የደን ሀብት ጥቅሙ እንዴት ይገለፃል? የከተማዋን የደን ሽፋን በማሳደግና በመጠበቅ ረገድ ምን እየተሰራ ይገኛል? የሚለው የሁልጊዜ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በተቋሙ የደን ሀብት አጠባበቅ ቡድን መሪ አቶ አማኑኤል ሽብሩ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፣ ቡድን መሪው አያይዘውም፤ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የደን ሀብት ልማቱ በእጅጉ አድጓል። የደን ሀብቱ ጥሩ ይዞታ ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የደን ሽፋኑ ከነበረበት ሦስት በመቶ በብዙ ከፍ እንዲል ሆኗል። በዚህ ምክንያት ደርቀው የነበሩ ወንዞች መፍሰስ ጀምረዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የቀበና ወንዝ ዓመቱን ሙሉ ይፈስሳል፡፡ ተበክለው የነበሩ ወንዞች ንጹህ ሆነዋል። አዳዲስ ምንጮች እንዲፈጠሩም አድርጓል፡፡ በባለፈው 2017 ዓ.ም ክረምት አዳዲስ የተለያየ ቀለምና መጠን ያላቸው የአእዋፋት ዝርያዎች መጥተዋል፡፡ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ተሰደው የነበሩትም ተመልሰዋል፡፡

“በመዲናዋ የተለያዩ አካባቢዎች ወደ ኢኮ-ቱሪዝምነት (ሥነ ምህዳርን የጠበቀና የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ ቱሪዝምነት) ተለውጠዋል። ወጣቶች፣ አረጋዊያንና ህጻናትን ጨምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም ለመዝናኛነት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ለልደት ማክበሪያነት እየዋሉ ነው፡፡” የሚሉት አቶ አማኑኤል፣ የደን መኖር ከሰው ልጅ ህልውና ባለፈ ለእንስሳትና አጠቃላይ ለሥነ-ፍጥረታት አስፈላጊ እንደሆነ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ቡድን መሪው ገለጻ፣ ለም አፈር እንዲፈጠር መሬት በራሷ ጊዜ መብላላት አለባት፡፡ ለመብላላት ባክቴሪያ መኖር አለበት፡፡ ባክቴሪያ ሊመጣ የሚችለው እርጥበትና የተወሰነ ሙቀት ተመጣጥኖ ሲመጣ ነው፡፡ እርጥበት ብቻ ከበዛ ፍጥረታት አይኖሩም፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከተማዋ ውስጥ ያሉት ወንዞች ተበክለው ነበር፡፡ ከፍተኛ መጨናነቅ ነበረባት፤ ምክንያቱም የደን ቦታዎች በሰዎች ተይዘው ስለነበር፡፡ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ትራንስፖርት አለ፡፡ ከትራንስፖርት የሚመነጨው ካርቦንዳይኦክሳይድ ለነዋሪዎች ምቾት አይሰጥም፡፡ ሰው መግባት የማይችልባቸው ጫካ የነበሩ ስፍራዎች ውስጥ የነበሩት እጽዋቶች ቀጭጨው ነበር፡፡ ምንም አይነት እንክብካቤ አይደረግላቸውም ነበር፡፡ ከዚህ ባለፈ በህገ ወጥ መንገድ ይጨፈጨፉ ነበር። በዚህም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አይሰጡም ነበር፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ደኖች የሚገኙበትን ስፍራ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ የላይኛው ተፋሰስና የታችኛው ተፋሰስ በሚል፡፡ የላይኛው ተፋሰስ የሚገኘው ከአንቆርጫ የካ ተራራ ጀምሮ በእንጦጦ ተራራ አድርጎ እስከ ቃሌ ተራራ አስኮ ድረስ የሚሄድ ነው፡፡ ይህም በክፍለ ከተማ ደረጃ ለሚ ኩራ፣ የካ፣ ጉለሌ የሚገኙበት ነው፡፡ የታችኛው ተፋሰስ በመባል የሚታወቁት አካባቢዎች ደግሞ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ ኮልፌ ቀራኒዮ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች ናቸው። በላይኛው እና ታችኛው ተፋሰስ ተቆርጠው በሚሸጡ ዛፎች መካከል የዋጋ ልዩነት አለ፡፡ ለማገዶ እና ለኮንስትራክሽን በሚውሉት ላይም በተመሳሳይ የዋጋ ልዩነት አላቸው። ዋጋቸው ተመን ይወጣላቸዋል፡፡ መንግስት በሚሸጥበት ወቅት የዋጋ ተመን የሚያወጣው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡ የዋጋ ተመኑን ለመወሰን ዛፉ የሚገኝበት ስፍራ እና የሚሰጠውን አገልግሎት ይወስናል፡፡ በታችኛው ተፋሰስ አካባቢ ውሀ ስለሚንጣለልና አብዛኛውን ጊዜ ረግረጋማ በመሆኑ የሚበቅሉት ዛፎች ረጃጅም ናቸው። ዛፎቹ በዓመት ከስድስት ወራት በላይ ውሃ ሊያገኙ ይችላሉ። እንጦጦ አካባቢ ደግሞ በተቃራኒው ተራራማ በመሆኑ ዝናብ ሲዘንብ ወደ ወንዝ ስለሚወርድ በቂ ውሀ እንደማያገኙ ገልጸዋል፡፡

እንደ ቡድን መሪው ገለጻ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የተለመደው የእጽዋት አይነት ባህር ዛፍ ነው፡፡ እንደ ወይራ ዝግባ ያሉ የሀገር በቀል ዛፎች የውበት ሳይሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ዛፎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ አፈር እንዳይሸረሸርና እንዳይናድ ውሃ አቁረው የመያዝ፣ ከሌላ አካባቢ ውሃ ስበው የማምጣትና በረሀማነትን ተቋቁመው የመቆየት ባህሪ አላቸው፡፡ የአፈር ለምነትንም ይጠብቃሉ፡፡ ባህር ዛፍ ግን ውሃ የመምጠጥ፣ ምንጮችን የማድረቅ፣ የአፈር ለምነትን የመቀነስ ባህሪ አለው። ስሩ ትልቅ በመሆኑ እየተቆረጠ ሲሄድ ራሱን የመተካት ባህሪ አለው፡፡ ከብዝሀ-ህይወት እና ሥነ-ምህዳር አንጻር የሀገር በቀል ዛፎች የተሻሉ ናቸው፡፡ በዚህም ከተማ አስተዳደሩ እነዚህ ሀገር በቀል ዛፎች እንዲስፋፉ የማድረግ እቅድ አለው፡፡ በሂደት ባህር ዛፍ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አኳያ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ሳይሆን መቀነስና ከሌሎች ሀገር በቀል እጽዋቶች ጋር የማመጣጠን ስራ ይሰራል፡፡

የደን መጨፍጨፍ እንዳይከሰት ዘላቂ መፍትሄ ከማበጀት አንጻር እየተሰራ ያለውን ስራ ቡድን መሪው ሲገልጹ፤ በፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የደን አዋጅ ቁጥር 1065/2010 ወጥቶ ተፈጻሚ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ ይህ አዋጅ ከመፍቀድ እስከ ተጠያቂነት ድረስ ያለውን ሰፊ ኃላፊነት የሰጠ ነው። አዋጅ ከማውጣት በተጨማሪም “የኢትዮጵያ ደን ልማት” የሚል መስሪያ ቤት እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡ የደን ልማትም ከአዋጁ ላይ ደንብ 544/2016 አውጥቷል፡፡

ከእነዚህ ከወጡት አዋጅና ደንብ ላይ ደግሞ የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የዛፍ መቁረጥ፣ ማዘዋወርና የደን ውጤቶች እንቅስቃሴ የይለፍ ፈቃድ አሰጣጥ 86/2016 መመሪያ አውጥቷል። በመመሪያው መሰረት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ተግባሩ የመከታተልና የመቆጣጠር ስራ ነው፡፡ ስለሆነም በየክፍለ ከተማው የሚደረጉ ህገ ወጥ የዛፍ ቆረጣ ይቆጣጠራል፡፡ ለማልማት ስልጣን የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፣ የጉለሌ እጽዋት ማዕከል እና ሌሎች ፓርኮች ሲሆኑ ተቋማቱ በተገቢው ሁኔታ ያለማሉ ወይንስ አያለሙም የሚለውን ከመከታተልና ከመቆጣጠር ስራ ባለፈ የመደገፍ ስራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም ባለስልጣኑ ከተማ ውስጥ ለአካባቢ ጥበቃ የሚሆኑ ሊተከሉ የሚችሉ እጽዋቶች ምን አይነት መሆን እንዳለባቸው ምክር ይሰጣል። በግለሰቦችና በመንግስት በኩል ያሉ የ“ይገባኛል” ጥያቄዎችን ይቆጣጠራል። ለምሳሌ፡- የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ካርታ እንዲያወጣ፣ የመንግስት ደን ወደ መንግስት ደን ይዞታ እንዲገባ፣ የግለሰቦች ደግሞ ለግለሰቦች እንዲሆን የይዞታ ማረጋገጫ እንዲይዙ ባለስልጣኑ ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፡፡ በመንግስት የለማ ዛፍ በህገ ወጥ መንገድ እንዳይቆረጥ ይቆጣጠራል፡፡ በሌላ መልኩ የመቁረጥ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ፍቃድ አሰጣጡ በሁለት መንገድ ይታያል፡፡ የመንግስት ደን አልሚው የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ስለሆነ በባለስልጣኑ የደን ልማት አስተዳደር ዛፍ በሚቆረጥበት ወቅት ለምሳሌ አንድ ክፍለ ከተማ ዛፍ የሚቆርጥ ከሆነ ምን ያህል ሄክታር ዛፍ እንደሚቆርጥ አጥንቶ በጽሑፍ ያዘጋጅና ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያስገባል፡፡ የሚቆረጠውም ባዘጋጀው እቅድና ጥናት መሰረት ነው፡፡ ይህንንም ባለስልጣኑ ለከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ያሳውቃል፡፡ ግለሰቦችና የግል ተቋማትም ፍቃድ በሚጠይቁበት ወቅት የመቁረጥ ፍቃድ ይሰጣሉ፡፡

እንደ አቶ አማኑኤል ገለጻ፣ ባለስልጣኑ ለመንግስት ደን ቀጥታ የመቁረጥ ፍቃድ አይሰጥም፡፡ ለከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ይጽፋል፡፡ ቢሮው በጥያቄው መሰረት ጨረታ ያወጣል፡፡ ጨረታውን ያሸነፈውን አካል መልሶ ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያሳውቃሉ፡፡ ዛፉ የሚቆረጠው ይህንን ሂደት ተከትሎ መሆኑ ክትትል ይደረጋል፡፡ በዚህ መልኩ ባለስልጣኑ ህገ ወጥ የደን ጭፍጨፋን እየተቆጣጠረ ይገኛል፡፡ ግለሰቦች በራሳቸው ላይ ያለ ዛፍ እንኳን ያለፍቃድ መቁረጥ አይችሉም። ምክንያቱም ዛፍ ያለፍቃድ በዘፈቀደ የሚቆረጥ ከሆነ የአካባቢ መጋለጥ እና የአየር ንብረት መዛባት ችግር፤ የብዝሀ ህይወት መመናመን ይፈጠራል። እነዚህ ሁኔታዎች ተጠንተው ነው ዛፍ እንዲቆረጥ ፍቃድ የሚሰጠው። የመብራትና የትራፊክ አደጋ እንዲሁም ግንባታን የማደናቀፍ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር ዛፍ መቁረጥ ክልክል ነው፡፡

## የቅጣት ደረጃዎች

ቅጣት ከመጣሉ በፊት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡ በ2016 ዓ.ም እና በ2017 ዓ.ም በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ለሚኖሩ 600 ለሚጠጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2018 ዓ.ም የጣውላና የዛፍ ነጋዴዎችን እንዲሁም ህገ ወጥ ዛፍ ቆረጣ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችንና በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ደላሎችን ከፖሊስና ደንብ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን ግንዛቤ ለማስጨበጥ እቅድ ተይዟል፡፡ በደን አዋጁ መሰረት የሚጣለው ቅጣትም ደረጃ አለው፤ ከፍተኛው 20 ሺህ ብር እና እስከ 10 ዓመት እስራት ያስቀጣል፡፡ ይህም ከባድ ቅጣት አጥፍቶ የተገኘ ነው። ትንሹ 5 ሺህ ብርና ሁለት ዓመት የእስር ቅጣት ነው፡፡ ካርታ ሳይኖረውና የራሱ ሳይሆን ሄዶ የመንግስትን ደን የጨፈጨፈ ሰው ከፍተኛ ወንጀል እንደፈጸመ ተወስዶ ከፍተኛው የቅጣት ደረጃ ይጣልበታል። በራሱ ይዞታ ላይ ራሱ ተክሎ የራሱ ይዞታ መሆኑን ሳያሳውቅ ቢቆርጥ አነስተኛ የቅጣት እርከን ማለትም እስከ 5 ሺህ ብርና ሁለት ዓመት እስር ቅጣት ይጣልበታል፡፡

በጥቅሉ ደን ለመዲናዋ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው፡፡ በአረንጓዴ አሻራ ሀገራዊ መርሃ ግብሩ መሰረትም በርካታ ስራ በመስራት አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ችላለች፡፡ በቀጣይም በተለይ መንከባከቡ ላይ በትኩረት መስራት ይጠበቅባታል መልዕክታችን ነው፡፡

# ማስታወቂያ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ኮ.059/97 ስም ሴሪ ቁጥር 148890 ፍቅርና ሠላም 16 የጋራ/ህ/የመ/ቤ/ኃ/የተ/የህ/ሥራ/ማህበር ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ቢያዝን ወልደአብ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 1487 በካርታ ቁጥር 18/27/15911/00 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማህደር ውስጥ መገኘት የነበረበት ካርታ ከነማህደሩ የጠፋ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞረው ብዙነሽ ተሰማ ዋሪዮ ስም በልደታ ክ/ማ የቀድሞ ወረዳ 03 የቀድሞ ቀበሌ 43 የቤት ቁጥር 1114/1115 በቀን 27/02/2012 የካርታ ቁጥር ል.5/151/18297/00 ሴሪ ቁጥር 0657124 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጀ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው እነ አበራሽ ሀብተየስ ደስታ እና አይናለም ሀብተየስ ደስታ ስም በልደታ ክ/ማ የቀድሞ ወረዳ 04 የቀድሞ ቀበሌ 40 የቤት ቁጥር 682/2 በቀን 07/08/2014 የካርታ ቁጥር ል.20076/ል.4/1/20076/00 ሴሪ ቁጥር 102410 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጀ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 272 በአቶ ደበበ ማሞ እሸቴ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር 7352 ሴሪ ቁጥር ---- የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 25/07/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ)የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 672 በወ/ሮ ወርቅነሽ ሙሉጌታ ወልደገብርኤል ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር 17397 ሴሪ ቁጥር ---- የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 25/07/2018 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ(አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

መለሰ ሊራንሶ ኤርሰዶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ /የይዞታ ልዩ መለያ/ ቁጥር AA000080126917 ሴሪ ቁጥር 0162331 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ መቅደላዊት በቀለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 045095/B/1 ሴሪ ቁጥር 0170487 የይዞታ ስፋት 150 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/21992/18 በቀን 24/07/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ለመኖሪያ አገልግሎት በካርታ ቁጥር 15/38/2382/22719/01 በሴሪ ቁጥር 036009 በአባይ አሰፋ ብርጫጋ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ብርሃን ፃአሩ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም ቤት የቤቱ ልዩ መለያ ቁጥር AA000051207336499010l0 የተሰጠበት ቀን 03/02/2015 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፓ/መ/ቁ/15/7299 በቀን 08/04/2018 ዓ.ም የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ፍቅሩ ቶሎሳ ካሳ እና የሺሀረግ ካሳ ጎፍታ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 11 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA00008111027 ሴሪ ቁጥር 0175226 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ክልል ውስጥ በወ/ሮ አልጋነሽ አሊ ይመር ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070401639/23101011l ሴሪ ቁጥር C 090360 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ/የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 23/07/2018 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦ/ሌ/9/101/4/1/59368/00 ሴሪ ቁጥር 1610748 በወ/ሮ በላይነሽ ሙሉጌታ ሀይሌ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 6 ቀበሌ 03 በአሁኑ ወረዳ 8 ቤት ቁጥር 136/137 ለሆነው ቤት በካርታ ቁጥር አከ-10/05/1/1096/አ.ካርታ በሴሪ ቁጥር 004174 በቀን 23/1/2004 በወ/ሮ አረጋሽ ጉራራ ስም የተመዘገበ የተነፃፃሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት በመብት ፈጠራ እና የይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 አንቀጽ 23 መሰረት የባለይዞታው የተነፃፃሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይገፄዋለው የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ አ/ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በደንቡ እና በአሰራሩ መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትኩ ሌላ የተነፃፃሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርትን ያማከለው የከተማ ልማት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በዘመናዊ የከተማ ልማት እቅድ ውስጥ፣ ስፖርት ከመዝናኛነት አልፎ የከተማዋን የልብ ትርታ የሚቆጣጠር መሰረታዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አንቀሳቃሽ ኃይል ሆኗል። የዛሬዎቹ ከተሞች የሰውን ልጅ እንቅስቃሴ፣ ማህበራዊ ትስስር እና የጤና ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችላቸውን አቅም የሚገነቡት፣ ስፖርትን ከከተማ መዋቅር ጋር በማዋሃድ ነው። ከተሞች የተጨናነቀ የህይወት ዘይቤ ለማቃለልና የዜጎችን ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ለመገንባት ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው።

እንደ ለንደን፣ ኒው ዮርክ እና ሲንጋፖር ያሉ የዓለም ታዋቂ ከተሞች የስፖርት መሰረተ ልማት በማስፋፋትና በከተማ መሃል የሚገኙ ግዙፍ የስፖርት ፓርኮችን በመፍጠር የዜጎችን ጤና ብቻ ሳይሆን የከተማቸውን ውበት እና ኢኮኖሚ ከፍ አድርገዋል። በተለይ በሲንጋፖር ከተማ የሚገኘው ሲንጋፖር ስፖርት ሃብ (Singapore Sports Hub) በዓለም ላይ ካሉ የስፖርት መሠረተ ልማቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ድንቅ የጥበብ ውጤት ነው።

ሲንጋፖር ስፖርትን ከከተማ ልማት ጋር እንዴት እንዳቀናጀች የሚያወሱት የከተማ ፕላን ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚያሳዩት የከተማዋ ስፖርት ሃብ እንዲሁ ስታዲየም ብቻ ሳይሆን፣ ስፖርትን ከንግድ፣ ከመዝናኛ እና ከማህበራዊ ህይወት ጋር ያቆራኘ 'የከተማ ውስጥ ከተማ' ነው። በ35 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ይህ ማዕከል፣ 55 ሺህ ሰዎችን የመያዝ አቅም ያለውን ብሔራዊ ስታዲየም ጨምሮ፤ የውሃ ዋና ማዕከል፣ የቤት ውስጥ ስታዲየም፣ የገበያ አዳራሾች እና የስፖርት ሙዚየምን በአንድ ላይ አቅፏል። ይህ ውህደት ተመልካቾች ለጨዋታ መጥተው በዚያው ግብይት እንዲያደርጉና እንዲዝናኑ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

የስፖርት ሀብ ዶት ኮም ገፀ ድር መረጃ እንደሚያሳየው ይህ የስፖርት ፓርክ ለሲንጋፖር ትልቅ የገቢ ምንጭ ነው። እንደ ወርልድ አትሌቲክስ ሻምፒዮና፣ የእስያ ጨዋታዎች እና ታዋቂ የሙዚቃ ኮንሰርቶችን በማስተናገድ በሺዎች የሚቆጠሩ ቱሪስቶችን ይስባል። ከስፖርታዊ ኩነቶች ባለፈ የንግድ ማዕከላቱ እና ምግብ ቤቶቹ ዓመቱን ሙሉ ክፍት በመሆናቸው፣ ለከተማዋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሞተር ሆኖ ያገለግላል።

የሲንጋፖር ስፖርት ፓርክ ለታዋቂ ስፖርተኞች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ዜጎች ክፍት ነው። በማዕከሉ ዙሪያ የሚገኙት የሩጫ መንገዶች፣ የብስክሌት መስመሮች እና በውሃ ዳርቻ ላይ የሚገኙ የመዝናኛ ስፍራዎች ነዋሪዎች የጤናማ ህይወት ዘይቤን እንዲከተሉ ያበረታታሉ። ቤተሰቦች ቅዳሜና እሁድን የሚያሳልፉበት፣ ወጣቶች የሚለማመዱበት እና አረጋውያን የእግር ጉዞ የሚያደርጉበት የጋራ የመገናኛ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።

ዛሬ ላይ አዲስ አበባም አዲስ የስፖርት ፓርክ በመገንባት ይህንን ጎዳና ተከትላለች። በ5 ነጥብ 7 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈውና በኦሎምፒክ መድረክ ለኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኙ 15 አትሌቶችን የሚዘክሩ የክብር ሐውልቶች በፓርኩ መሃል ያቆመው ይህ ፓርክ ሰሞኑን ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡ የኦሎምፒክ ደረጃውን የጠበቀ የመዋኛ ገንዳ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የእግር ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ እና የሜዳ ቴኒስ መሰረተ ልማቶች፣ የ800 ሜትር የሩጫ ትራክ ማዕከሉ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ተደርጎ ተገንብቷል፡፡

ፕሮጀክቱ ከላቀ የስፖርት አገልግሎት ባለፈ፣ በልማቱ ምክንያት ለተነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች የኢኮኖሚ አቅም የሚሆኑ 105 አዳዲስ የንግድ ሱቆች እና 3 ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል ሰፊ ፕላዛ ይዟል። እንደዚሁም በአንድ ጊዜ 300 መኪናዎችን የሚይዝ ባለ ሁለት ወለል የምድር ቤት መኪና ማቆሚያ በውስጡ አካቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሰሞኑን የተመረቀው ዘመናዊ የስፖርት ፓርክ፣ የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ ለነዋሪዎቿ ጤናማና ንቁ የአኗኗር ዘይቤን በማምጣት ረገድ ትልቅ ምዕራፍ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ፕሮጀክት በከተማ ልማትና በስፖርት መሰረተ ልማት መካከል ያለውን ጥብቅ ቁርኝት በተግባር ያሳየ ሲሆን፣ በተለይም ወጣቶችና የስፖርት አፍቃሪዎች በቅርብ ርቀት ደረጃቸውን የጠበቁ ማዘውተሪያዎችን እንዲያገኙ ያስችላል።

> **ፓርኩ ዘመናዊ የእግር ኳስ ሜዳዎችን፣ የቅርጫት ኳስና የቮሊቦል መጫወቻዎችን እንዲሁም የሩጫና የብስክሌት መሄጃዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ የያዘ ነው**

ፓርኩ ዘመናዊ የእግር ኳስ ሜዳዎችን፣ የቅርጫት ኳስና የቮሊቦል መጫወቻዎችን እንዲሁም የሩጫና የብስክሌት መሄጃዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ የያዘ ነው። ይህ መሰረተ ልማት ነዋሪዎች ከስራ ጫና ወጥተው የሚያርፉበት፣ አካላዊ ብቃታቸውን የሚያሳድጉበትና ማህበራዊ ትስስራቸውን የሚያጠናክሩበት 'የከተማዋ ሳንባ' ሆኖ ያገለግላል። ከዚህም ባለፈ፣ ፕሮጀክቱ የአካባቢውን ውበት ከመጠበቅና አረንጓዴ ልማትን ከማስፋፋት አኳያ ለከተማዋ የረጅም ጊዜ እድገት የላቀ ፋይዳ አለው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ፓርኩን መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንደገለፁት "የከተማችንን እድሳት ለማፋጠን እና የዜጎቻችንን ክብር ለመመለስ የገባነውን ቃል አንዱ ማረጋገጫ የሆነውን የአዲስ ስፖርት ፓርክን በይፋ መርቀን ከፍተናል" ብለዋል፡፡

በ5 ነጥብ 7 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ይህ ፕሮጀክት፤ በኦሎምፒክ መድረክ ለሀገራችን የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኙ 15 አትሌቶችን የሚዘክሩ የክብር ሐውልቶችን በፓርኩ መሃል በማቆም፣ የጀግኖቻችን ታሪክ ለተተኪ ትውልድ ስፖርተኞች ተምሳሌት ሆኖ እንዲቀጥል ያደርጋልም ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

የአዲ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በምረቃው ወቅት እንደገለጹት፣ እንዲህ ያሉ ፕሮጀክቶች የከተማዋን ነዋሪዎች የኑሮ ጥራት ለማሻሻል ካላቸው ቁርጠኝነት የሚመነጩ ናቸው።

ከንቲባዋ ባስተላለፉት መልዕክት፣ "ይህ የስፖርት ፓርክ ለወጣቶቻችን የስፖርት መክሊታቸውን የሚያሳድጉበት ብቻ ሳይሆን፣ ጤናማና አምራች ትውልድ የምንገነባበት ማዕከል ነው" ብለዋል።

ትውልዱን ለመገንባት የያዝነውም ራዕይ የምንተገብርበት ስፍራ ጭምር ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ ኢትዮጵያን በዓለም ደረጃ ስሟን የሚያስጠሩ ወጣቶች የሚፈጠሩበትና የሚሰለጥኑበት ቦታ ስለመሆኑም ገዋፀዋል፡፡ አክለውም፣ ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የሚከናወኑ የኮሪደር ልማትና መሰል የልማት ስራዎች ስፖርትንና ጤናማ እንቅስቃሴን ማዕከል ማድረጋቸውን እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል።

በአዲስ ስፖርት ፓርክ የምረቃ እና ጉብኝት መርሐ ግብር ላይ የተገኘው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በበኩሉ፣ የልማት ስራው ለሀገር ያለውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አስመልክቶ ምስክርነቱን ሰጥቷል። አትሌት ቀነኒሳ በተለያዩ የዓለም ሀገራት ለውድድር በሚጓዝበት ወቅት በከተሞቻቸው ውስጥ ትላልቅ ፓርኮችና ማህበረሰቡ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግባቸው ሜዳዎች ከፍተኛ የቅናት ስሜት ያሳድሩበት እንደነበር ገልጿል። እንደ አትሌቱ ገለጻ፣ ስፖርት የአንድ ሀገር የጀርባ አጥንት ሲሆን፣ ይህም ዜጎች እንደ ስኳርና የደም ግፊት ካሉ ስር የሰደዱ በሽታዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ይረዳቸዋል ይላል።

በተጨማሪም ህዝቡ በጤና እጦት ምክንያት ለመድኃኒት የሚያወጣውን ወጪ የሚቀንስ ሲሆን፣ ሀገርም ለህክምና ግብዓቶች የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ እንድታድን በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጋ ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብሏል።

የስፖርት ጋዜጠኛ ኤፍሬም የማነህ በማህበራዊ ትስስር ገፁ ባሰፈረው ጽሑፍ እንዳለው በየሰፈሩ በብዛት እየተሰሩ ካሉ ምቹ ሜዳዎች ባሻገር እንደ ካዛንቺሱ የስፖርት ፓርክ ዐይነቶቹ የነገ የትውልድ አሻራ ህያው ቀለሞች ሆነው ይጠቀሳሉ ይላል። በዓለም መድረክ የኩራታችን ሚስጥር የሆኑ ጀግኖች አትሌቶቻችንን በአግባቡ የሚዘክር እና ለትውልድ መነቃቃት በሚሆን መልኩ ያውም መሬት ወርዶ መታየቱ ኮኮቦችን ለመፈጠር ታላቅ ሚና አለው ይላል፡፡

ይህ የስፖርት ፓርክ ከስፖርታዊ እንቅስቃሴ ባለፈ ሰፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን ይዟል። በተለይም በከተማዋ የሚስተዋለውን የማዘውተሪያ ስፍራዎች እጥረት በመቅረፍ፣ ወጣቶች ጊዜያቸውን በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲያሳልፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ፓርኩ ለተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችና ማህበራዊ ኩነቶች መድረክ በመሆን የከተማዋን የ24 ሰዓት እንቅስቃሴ (24-hour cycle) የሚያነቃቃ ሲሆን፣ ይህም ለአካባቢው አነስተኛ ንግዶች መነቃቃትና ለአዳዲስ የስራ እድሎች ፈጠራ የራሱን አዎንታዊ አሻራ ያሳርፋል።



ፎቶ- ከፋይል
በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ካዛንቺስ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የተገነባው የስፖርት ፓርክ ከፊል ገፅታ


ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
ቴሌብር
telebirr
እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው
በሰላም አጸረሳችሁ!
ሚያዝያ 2018 ዓ.ም